አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

**ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፭**
**አዲስ አበባ** ከመጋቢት 4 ቀን **፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**31st year No. 55**
**Addis Ababa፣ February 25th , 2023**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር 1፻፶/2ሺ!5**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሠን የወጣ ደንብ**

**ገጽ----------------------------- ፪ሺ9)!3**

**CONTENTS**

**REGULATION NUMBER 150/2023**
**A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATION, PROCEDURE, AND PARAMILITARY EMPLOYEES' MANAGEMENT OF THE CODE ENFORCEMENT AUTHORITY OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT**

**Page--------------------------------------- 2913**

**ደንብ ቁጥር 1፻፶/2ሺ!5**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አደረጃጀት፣ አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ለመወሠን የወጣ ደንብ**

የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጠዉን ሥልጣንና ተግባራት በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ አደረጃጀት፣ አሠራርን እና የባለሥልጣኑን የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**REGULATION NUMBER 150/2023**

**A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATION, PROCEDURE, AND PARAMILITARY EMPLOYEES' MANAGEMENT OF THE CODE ENFORCEMENT AUTHORITY OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT**

**WHEREAS,** it has been found necessary to amend the regulation for the organization, procedure, and management of the paramilitary employees of the authority in order to properly carry out the power and duties entrusted to the code enforcement authority as per the proclamation;

**ያንዱ ዋጋ..........**
**Unit price..........**

**አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭**
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸4/2ሺ!4 አንቀፅ ፺1 እና አንቀጽ ፵7 ንዑስ አንቀጽ (!7) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1 አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣንን አደረጃጀት አሰራር እና የፓራሚሊተሪ ሠራተ

ኞች አስተዳደር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 1፻፭/2ሺ!5" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1 " **ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2 "**አስተዳደር**'' ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3 "**አዋጅ**'' ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፸4/2ሺ!4 ነው፤
4 "**ባለስልጣን**'' ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ነው፤
5 "**ጽሕፈት ቤት**"" ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የተደራጀ የደንብ ማስከበር ጽሕፈት ቤት ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with 91 and Sub-Article (17) of Article 47 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## Part One

## General Provisions

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as: **"The Addis Ababa City Government Code Enforcement Authority Organization, Procedure, and Paramilitary Employees Management Determination Regulation Number 105/2023."**

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the city of Addis Ababa;
2. **"Government"** means the Addis Ababa city government;
3. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021;
4. **"Authority"** means the Addis Ababa city government Code Enforcement Authority;
5. **"Office"** means the Code Enforcement Office, being established at the sub-city and woreda level;

6 **"ፓራሚሊታሪ"** ማለት በአሰራር፣ በአስተዳደር፣ በስልጠና ከፊል ወታደራዊ ይዘትን ያካተተ እና በሥነ-ምግባር የተቃኘ ደንብን የሚያስከብር አደረጃጀት ነው፤

7 **"ፓራሚሊተሪ ኦፊሰር"** ማለት ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን ከፊል ወታደራዊ ስልጠና ወስዶ ያጠናቀቀ እና የደንብ መተላለፍ ድርጊቶችን የሚከላከል፣ እርምጃ የሚወስድና የሚያስወስድ ባለሙያ ነው ፣

8 **"የሽፍት አስተባባሪ"** ማለት በባለስልጣኑ በየደረጃው ባለው መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ሽፍት መሪዎችን የሚመራ ነው፤

9 **"ሽፍት መሪ ማለት"** በባለስልጣኑ ስር በየደረጃው ባለው መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን የሚመራ መሪ ነው፤

!. **"የደንብ መተላለፍ ቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር"** ማለት በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ድርጊት፣ ለመለየት፣ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ እርምጃ ለመዉሰድ እና ለማስወሰድ የተቀጠረ ወይም የተመደበ ፓራሚሊተሪ ኦፊሰር ነው፤

**!1. "የደንብ መተላለፍ ቅድመ መከላከል ኦፊሰር" ማለት** በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ አስቀድሞ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶች ለህብረተሰቡ ስለ ደንብ መተላለፍ ተግባራት ግንዛቤ የሚሰጥ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር ነው፤

**!2. "ግብረ-ሀይል"** ማለት ከወረዳው ጽህፈት ቤት አቅም በላይ የተፈጸሙ የደንብ መተላለፎችን በመለየት እርምጃ የሚወስድ፣ የሚያስወስድና የሚያስተባበር አካል ነው፣

6. **"Paramilitary"** means an ethically oriented organization that enforces codes having a paramilitary nature in its procedure, administration and training;

7. **"Paramilitary Officer"** means a professional who has completed the semi-military training provided by the authority and prevents code violations, take or cause the taking of action against the thereof;

8. **"Shift Coordinator"** means an individual that leads the shift coordinators at every structural level of the authority;

9. **"Shift Leader"** means a leader who directs paramilitary officers at various levels of the structure under his authority;

10. **"Code Violation Controlling and Measure Taking Officer"** means a paramilitary officer who is hired or assigned to identify, prevent, control, take or cause the taking of measures on those acts of code violations that are indicated in this Regulation;

11. **"Code Violation Pre-prevention Officer"** means a paramilitary officer that carries out awareness creation activities for society about code violation actions in advance through various mechanisms to prevent the occurrence of code violation acts that are indicated in this Regulation;

12. **"Task force"** means an organ that identifies code violations that are beyond the mandate of the woreda office and take or causes the taking of measures and coordinates same;

!3. **"ደንብ ተላላፊ"** ማለት አግባብ ባለው ባለሥልጣን የወጣውን ሕግ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ መመሪያ ወይም የጥንቃቄ እርምጃ የጣሰ ሰው ነዉ፤

!4. **"በሕገ-ወጥ መንገድ መሬትን መያዝ ወይም መሬትን መውረር''** ማለት የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣዉን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በመተላለፍ አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል ፈቃድ ሳያገኝ መሬትን መያዝ ወይም መውረር ነው፤

!5. **"ሕገ-ወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት''** ማለት አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል በሕጋዊ መንገድ ከተሰጠው ቦታ በተጨማሪነት አዋሳኙ የሆነዉን መሬት አስፋፍቶ መያዝ ነው፤

!6. **"ሕገ-ወጥ ግንባታ''** ማለት በሕገወጥ መንገድ መሬትን በመያዝ ወይም ሕገወጥ የመሬት ይዞታ በማስፋፋት በተያዘ ቦታ ወይም በሕጋዊ ይዞታ ላይ ያለ ግንባታ ፈቃድ በእንጨት፣ በፕላስቲክ፣ በሸራ፣ በብሎኬት፣ በብረት ወይም በማናቸዉም ቁሳቁስ ከላይኛዉ የመሬት ገጽታ በላይም ሆነ በታች የተገነባ ማንኛውም ግንባታ ሆኖ የመጠን፣ የቁስም ሆነ የዲዛይን ለዉጥ ያደረገ ሲሆን እድሳትንም ያካተተ ነው፤

!7. **"መንገድ'' ማለት** በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ዋና መንገዶች፣ መለስተኛ መንገዶች፣ መጋቢ መንገዶች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የመንደር መንገዶች፣ አደባባይ ወይም የአደባባይ ዙሪያዎች፣ የመንገድ አካፋይ ደሴቶች፣ በመንገድ ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛ ወይም የብስክሌት ማስተላለፊያዎች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ ድልድይ ወይም የጎርፍ ማስወገጃ መስመሮችን ወይም

13. **"Transgressor"** means a person that violates the laws, regulations, orders, directives, or cautionary measures that are issued by the relevant authority;

14. **"Illegal Land Seizure or Land Grabbing"** means the seizure of land without having a permit from the relevant organ of the city government or land grabbing by violating the proclamation, regulation, or directives that are issued regarding the possession of urban land through a lease;

15. **"Illegal Expansion of Land Possession"** means the expansion and seizure of neighbouring land in addition to the land that was entitled legally by the relevant organ of the city government;

16. **"Illegal Construction"** means any construction on the surface of land or underneath using wood, plastics, canvas, bricks, metal, or any other material through illegal land seizure or illegal expansion of land possession or without getting a construction permit on a legal land title; and it includes the change in size, material, or design as well as refurbishment;

17. **"Road"** means principal roads, arterial roads, sub-arterial roads, collector roads, village roads, roundabouts, road medians, pedestrian roads or bicycle ways at the left and right sideways, railroads, bridges, or sewerage lines that are found in the city,

በከተማው መሪ ፕላን መሠረት ለመንገድነት የተያዘን ቦታ ይጨምራል፤

!8. **“ሕገ-ወጥ የመንገድ ላይ ንግድ (የጎዳና ላይ ንግድ)’’** ማለት በከተማ አስተዳደሩ በተወሰኑ ቀን እና ሰዓት በመንገድ ላይ ለመነገድ ከተፈቀደባቸው መንገዶች ውጪ በሌላ በማንኛውም መንገድ ወይም ቦታ ላይ የሚካሄድ ማንኛውም የንግድ ሥራ ነው፤

!9. **“በረንዳ ንግድ’’** ማለት ማንኛውም ሰው በህጋዊ መንገድ ለንግድ አገልግሎት ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ አዋሳኝ በሆነ መንገዶች ወይም ቦታ ላይ የንግድ ተግባር ማከናወን ነው፡

፳. **“ህገ-ወጥ የውጭ ማስታወቂያ’’** በመንገድ ላይ ባለ የትራፊክ መብራቶች፤ ምልክቶች፤ ፖሎች በድልድች፤ በእግረኛ መከላከያ እና በሌሎች አጥሮች ያለፍቃድ ማንኛውንም የውጭ ማስታወቂያ፤ በራሪ ወረቀት፤ ብሮሸር መለጠፍ፤ ማንጠልጠል ወይም ማሰራጨትን የሚያጠቃልል ነው፤

፳1. **“ደረቅ ቆሻሻ’’** ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከጋራዥ፣ ከመንገድ ፅዳት፣ ከግንባታ፣ ከግብርና፣ ከመሬት ቁፋሮ ወይም ከጠቅላላው የሕብረተሰቡ ሥራዎች ወይም በእንስሳት ምክንያት የሚፈጠር፣ ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር ቆሻሻ ነው፤

፳2. **“ፍሳሽ ቆሻሻ’’** ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከጋራዥ፣ ከማንኛውም መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚወጣ የልብስ፣ የምግብ እቃዎች፣ የመጠጥ ዕቃዎች እጣቢ፣ አተላ፣ አምቡላ፣ የመፀዳጃ ቤት ፈሳሽ፣ የእንስሳት ማደሪያ ፍሳሽ፣ መርዛማ ንጥረ ነገር ያዘለ ወይም ያላዘለ ፍሳሽ የመሳሰሉት ነው፤

or it includes a plot of land reserved for road purpose in the master plan of the city;

18. **“Illegal Street Vending”** means any business activity which is undertaken on any road or place except the roads that are permitted by the city government to carry out same for specified days and time;

19. **“Veranda Business”** means undertaking a business activity on adjoining roads or spaces by an individual beyond the spaces that are permitted as per the law to carry out a business activity;

20. **“Illegal Outdoor Advertisement”** means the posting, hanging, or distribution of any outdoor advertisements, fliers, or brochures on traffic lights, road signs, poles, bridges, pedestrian barriers, and other fences without permission;

21. **“Solid Waste”** means solid and semi-solid wastes generated from households, businesses, industries, garages, road cleaning, construction, agriculture, earth excavation, or generally wastes that are generated from the activities of the society or animals;

22. **“Liquid Wastes”** means liquid waste generated by households, industries, garages, and governmental and non-governmental organizations such as laundry wastes, sanitary wastes, brewers' grains, latrine wastes, cattle barns liquid wastes, and similar others like poisonous and non-poisonous liquid wastes;

፳3. **"ልዩ ቆሻሻ''** ማለት ከመኖሪያ ቤት ፣ከንግድ ተቋማት ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የሚወጡ የቤት ቁሳቁስ የመኪና ልዩ ልዩ እቃዎች ፣ ባትሪ፣ ጎማ ፣ የመኪና ዘይት፣ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ፣ ምድጃ ፍሪጅ፣ የላውንደሪ መሳሪያዎች ቀለሞች፣ ወይም ሌሎች ትላልቅ እቃዎችና ለብቻቸው መሰብሰብና መወገድ ያለባቸው ወይም ከተለመደው የዕለት ተዕለት ቆሻሻዎች ለየት ያሉ ተብሎ በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚወሰኑ ቆሻሻዎችን የሚያጠቃልል ነው፤

፳4. **"አደገኛ ቆሻሻ"** ማለት የሚፈነዱ፤ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ፤ መርዛማ ነገሮች፤ ራዲዮአክቲቭ ቁሶች፤ ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፤ የደም ንኪኪ ያላቸው ሆነው ከኢንዱስትሪ፤ ከማምረቻ ተቋማት፤ ከጤና ተቋማት ወይም ከቤተ ሙከራ የሚወጡና በሰው፤ በእንስሳ፤ በእጽዋትና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ማንኛውም ቆሻሻ ነው፤

፳5. **"አዋኪ ድርጊት"** ማለት በባለቤትነት፣ በተከራይነት፣ ወይም በማናቸውም መልኩ በይዞታነት በያዘው ቦታ ወይም ቤት ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱን በሚያውክ አኳኋን በትምህርት ቤት ዙሪያ እስከ 200 ሜትር መጠነ ዙሪያ ክልል ውስጥ ቁማር እንዲጫወቱበት ወይም እዲያጫውቱበት፣ የመኝታ ቤት ንግድ አገልግሎት መክፈት፣ ፊልም እና ቪዲዮ ማሳየት፣ የቀንም ሆነ የሌሊት ጭፈራ መፈጸም፣ ማንኛውንም አይነት የአልኮል መጠጥ መሸጥ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

23. **"Different Wastes"** means wastes generated from houses, business institutions, or other organizations like house utensils, vehicle spare parts, batteries, tire, vehicle lubricants, electronics, stoves, refrigerators, paints, or other large materials and that should be collected and disposed separately or different from the day to day regular wastes which will be determined by the sanitary management agency;

24. **"Dangerous Wastes"** means any explosive, combustible, poisonous wastes, radioactive material, various chemicals, and wastes generated from industries, manufacturing institutions, health institutions, or laboratories having blood contact which cause harm to human beings, animals, plants, and the environment;

25. **"Disturbing Action"** means undertaking or causing the undertaking of gambling, providing pension service, film or video watching places, day and night clubs, selling alcoholic drinks, and carrying out similar other activities within 200 meters radius of a school that disturbs the teaching and learning process on a place or house which is possessed and managed throughownership, lease, or any other form;

፳6. **“ጫት ማስቃም”** ማለት በባለቤትነት፣ በተከራይነት፣ ወይም በማናቸውም መልኩ በይዞታነት የያዘውን ወይም የሚያስተዳድረውን ቦታ ወይም ቤት ውስጥ ገቢ ለማግኘት ወይም ለሌላ አካል ገቢ ለማስገኘት ጫት እንዲቃምበት ማድረግ ነው፤

፳7. **“ሺሻ ማስጨስ”** ማለት በባለቤትነት፣ በተከራይነት፣ ወይም በማናቸውም መልኩ በይዞታነት የያዘውን ወይም የሚያስተዳድረውን ማንኛውንም ቦታ ወይም ቤት ውስጥ ሺሻ ማስጨስ ወይም ለሌላ አካል ሺሻ እንዲጨስበት ማድረግን ያጠቃልላል፤

፳8. **“ሰርቪላንስ (ክትትል)”** ማለት የደንብ መተላለፍ መነሻ ምክንያት ወይም ምንጭ የሆኑትን ተግባራት ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ የሚለይ ነው፤

፳9. **“የሥራ መደብ”** ማለት በፓራሚሊተሪ የሚተዳደሩ ሰራተኞች ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲያከናውኑ በባለስልጣኑ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

፴. **“የማዕረግ ዕድገት”** ማለት በፓራሚሊተሪ የሚተዳደሩ ሠራተኞችን ከያዘው ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ማሳደግ ነው፤

፴1. **“የትርፍ ሰዓት”** ማለት ለፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ከተወሰነው መደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በተጨማሪነት እንዲሰራ የሚደረግ ሰዓት ነው፣

፴2. **“የትርፍ ሰዓት ጊዜ ክፍያ”** ማለት የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ከተወሰነው መደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በእረፍት ጊዜያቸው የትርፍ ሰዓት ሥራ ሲሰሩ የሚከፈል ክፍያ ወይም የማካካሻ እረፍት ነው፤

26. **“Allowing Chat Chewing”** means allowing chat chewing to get an income for oneself or to generate an income for others on a place or house which is possessed and managed through ownership, lease, or any other form;

27. **“Allowing Shisha Smoking”** means allowing shisha smoking or permitting others to carry out shisha smoking in a place or house which is possessed and managed through ownership, lease, or any other form;

28. **“Surveillance”** means an activity that identifies the actions that could be a cause or source of code violation secretly;

29. **“Working Position”** means the duties and responsibilities given by the authority for employees under the paramilitary management to be undertaken on a full-time basis;

30. **“Rank Promotion”** means the promotion of employees under paramilitary management from one's current status to the next level;

31. **“Overtime"** means an extra working time that the paramilitary employee is caused to do in addition to the determined regular working hours;

32. **“Overtime Pay”** means a payment or compensation leave to be paid or given to a paramilitary employee when he works overtime or in his leisure time more than the determined working hours;

፴3. **"ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫው ያለክፍያ የመጓጓዣ ተሽከርካሪ ተመድቦላቸው አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግበት አሰራር ነው፤

፴4. **"ድልድል"** ማለት አንድን የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ወይም ከፍ ባለ ደረጃና ደመወዝ ወይም በሠራተኛው ስምምነት ዝቅ ባለ ደረጃ መድበ ማሠራት ነው፣

፴5. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

33. **"Free Transportation Service"** means a system that ensures paramilitary employees get free transportation service at work opening and closing hours through assigning transportationvehicles;

34. **"**Deployment" means the assigning of a paramilitary employee to a similar position and salary scale or a higher position or salary scale or a lower position, as per his consent, and causing him to work;

35. **"Person"** means any natural or juridical person.

**3 ስለ ጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**4 ዓላማ**

ባለስልጣኑ የተሰጠውን ተግባር እና ኃላፊነትን በተገቢው መልኩ ለመወጣት የሚያስችል ጠንካራ አደረጃጀትና አሰራርን በመፍጠር በከተማዋ እየተስተዋለ የሚገኘውን የደንብ መተላለፎችን እና ተያያዥ ህገ-ወጥ ተግባራትን ለመከላከል ብሎም እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ቅጣትን በመወሰን ከተማዋ ለነዋሪዎቿ ምቹ እና የህግ የበላይነት የሰፈነባት ማድረግ ነው፡፡

**3. Gender Expression**

In this Regulation, any expression in the masculine shall include the feminine.

**4. Objective**

Create a strong organization and procedure that enables the authority to appropriately undertake its duties and responsibilities to prevent and take measures on code violations which are exhibited in the city by determining fines that enable to achieve the thereof and to make the city conducive for its residents and ensure rule of law.

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ ተጠሪነት እና ተግባርና ኃላፊነት

**5 አደረጃጀት**

ባለስልጣኑ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

1 በማዕከል ደረጃ፡-

ሀ) ዋና ሥራ አስኪያጅ፣

ለ) ምክትል ሥራ አስኪያጆች፣

ሐ) የባለሥልጣኑ ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣ እና

መ) አስፈላጊ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

2 በክፍለ ከተማ ደረጃ፡-

ሀ) የክፍለ ከተማ ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣

ለ) አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

3 በወረዳ ደረጃ፡-

ሀ) የወረዳው ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ኃላፊ፣

ለ) አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

**6 ተጠሪነት**

1 የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ነው፤

2 የክፍለ ከተማ ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለክፍለ ከተማው ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ነው፤

3 የወረዳው ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለወረዳው ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

## Part Two

## Organization, Accountability, and Duties and Responsibilities

**5. Organization**

The authority shall have the followingorganization:

1. At the city level:-
   A. General Manager;
   B. Deputy Managers;
   C. Head of the Office of the Authority; and
   D. The necessary departments and employees.
2. At the sub-city level:-
   A. Head of the code enforcement office of the sub-city;
   B. The necessary departments and employees;
3. At the woreda level:-
   A. Head of the code enforcement office of the woreda;
   B. The necessary departments and employees.

**6. Accountability**

1. The authority shall be accountable to the Peace and security administrationbureau;
2. The code enforcement office of the sub-city shall be accountable to the peace and security administration office of the sub-city;
3. The code enforcement office of the woreda shall be accountable to the peace and security administration office of the woreda.

**7 የባለስልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

በአዋጁ አንቀጽ !4 ንዑስ አንቀጽ (2) ፣ (3) እና አንቀጽ !5 የተደነገገው የወል ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1 ባለስልጣኑን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
2 በአዋጁ እና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤
3 የባለስልጣኑን ስትራቴጂካዊና ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4 የፓራሚሊተሪ ሠራተኞችንም ሆነ ሌሎች የባለሥልጣኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ኃላፊዎችን እንዲሾሙ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፀድቅ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
5 ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀት እና በአዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የአስተዳደሩን የፋይናንስ ሕግ ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ ሀብትና ንብረት ያስተዳድራል፤
6 ባለሥልጣኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነት ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

**7. Duties and Responsibilities of the General Manager of the Authority**

The General Manager shall, without prejudice to the joint responsibilities specified under Sub-Article (2) and (3) of Article 14 and Article 15 of the Proclamation, have the following duties and responsibilities:

1. Superiorly lead and coordinate the authority;
2. Enforce the duties and responsibilities of the authority given by the Proclamation and other relevant laws;
3. Prepare the strategic and annual plan and budget of the authority; implement same upon approval;
4. Hire, manage, and dismiss paramilitary employees and other supporting staff employees of the authority as per the relevant laws; submit the appointment of the heads of the code enforcement offices of the sub-city and woreda to the concerned organ; follow up the implementation of the thereof upon approval;
5. Effect payments according to the approved budget and prepared working plan of the authority based on the finance laws of the city administration; manage resources and properties;
6. Represent the authority in its dealing with third parties;

7 የባለሥልጣን ጠቅላላ የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ተጠሪ ለሆነለት አስፈፃሚ አካል ያቀርባል፤

8 ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

9 በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰሮችን እና በደንብ ተላላፊዎች በይግባኝ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲ ዓላማን ለማስፈጸም የሚያስችል ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**8 <u>የደንብ መተላለፍ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1 የባለስልጣኑን የደንብ መተላለፍ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፕሬሽናል ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

2 በስሩ የሚገኙትን ዳሬክቶሬቶችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር አሰራር መሠረት ይመዝናል፤ ሲጸድቅ እዉቅና ይሰጣል፤

3 ለሥራ የሚያስፈልገዉን በጀትና ግብአት ጥናት ላይ በመመስረት አጥንቶ ያቀርባል፤ ሲፈቀድለት በስራ ላይ ያውላል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

7. Prepare the overall plan implementation and financial report of the authority and present same to the executive organ to which it is accountable;
8. May delegate part of his powers and responsibilities to other officials and employees of the authority to the extent necessary for the effective performance of the activities of the authority;
9. Without prejudice to other laws, give final decisions on appeal complaints submitted by paramilitary officers and transgressors;
10. Carry out other activities that help to attain the objectives of the authority.

**8. <u>Duties and Responsibilities of the Code Violation Controlling and Measure-Taking Sector Deputy Manager</u>**

The deputy manager shall have, being accountable to the general manager, the following duties and responsibilities:

1. Superiorly lead and coordinate the code violation controlling and measure-taking operational activities of the authority;
2. Lead and coordinate the directorates under him; evaluate the thereof according to the relevant procedures of the citygovernment; provide recognition upon approval;
3. Study and present the budget and resources that are necessary for the work; implement same upon approval; follow up the execution of the thereof;

4 የዘርፉን ተልዕኮ ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችና ማንዋሎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤ በጥናት ግኝት መሠረት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ አተገባበሩን ይከታተላል፤

5 ለእርምጃ አወሳሰድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሚስጢራዊ በሆነ መልኩ በማዕከል በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና ወቅታዊ በማድረግ ለኦፐሬሽን ሥራዎች በግብዓትነት ያውላል፤

6 ከደንብ ማስከበር ጋር በተያያዘ የወጡ አዋጆችን፤ ደንቦችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

7 የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመቆጣጠር፣ በማስተባበርና በመምራት ዋና ሥራ አስኪያጁን ያግዛል፤

8 በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

9 **<u>የደንብ መተላለፍ ቅድመ መከላከል እና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግበርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1 ለደንብ መተላለፍ ተጋላጭ አካባቢዎች፣ መንስዔና የመፍትሄ አቅጣጫዎች በዳሰሳ ጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፤

2 የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመቆጣጠር፣ በማስተባበርና በመምራት ዋና ሥራ አስኪያጁን ያግዛል፤

3 የዘርፉን ተልዕኮ ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዳዲስ አሰራሮችና ማንዋሎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤ በጥናት ግኝት መሠረት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ አተገባበሩን ይከታተላል፤

4. Cause the study of new procedures and manuals that enable to achieve the mission of the sector; implement same as per the findings of the study; follow up the implementation of the thereof;

5. Collect, organize, and update confidential information at the central level that is necessary for the taking of measure and use same as input for operational tasks;

6. Follow up the implementation of proclamations, regulations, and directives that were issued in connection with code enforcement;

7. Assist the general manager through planning, organizing, controlling, coordination, and leading the activities of the authority;

8. Carry out other activities that are specifically delegated to him by the general manager.

9. **<u>Duties and Responsibilities of the Prevention and Training Sector Deputy Manager</u>**

The deputy manager shall have, being accountable to the general manager, the following duties and responsibilities:

1. Cause the identification of susceptible areas and causes for a code violation and their solutions through survey studies;
2. Assist the general manager through planning, organizing, controlling, coordination, and leading the activities of the authority;
3. Cause the study of new procedures and manuals that enable to achieve the mission of the sector; implement same as per the findings of the study; follow up the implementation of the thereof;

4 በስሩ የሚገኙትን ዳሬክቶሬቶችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ አግባብ ባለው የከተማው አስተዳደር አሰራር መሠረት ይመዝናል፤ ሲጸድቅ እዉቅና ይሰጣል፤

5 የደንብ መተላለፍን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

6 አዲስ ለሚቀጠሩ፣ ለሚመደቡ፣ ወይም በስራ ላይ ለሚገኙ ባለሙያዎች የፓራ-ሚሊተሪ ሠራተኞች ስልጠና እንዲያገኙ ያስተባብራል፤ ይተገብራል፤

7 መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በደንብ መተላለፍ ዙሪያ ላይ ስልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

8 ስለደንብ መተላለፍ ድርጊቶች መከላከል በህትመት፣ በመድረክና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መሰጠቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ያስተባብራል፤

9 የከተማዉ ነዋሪ በደንብ መተላለፍ መከላከል ዙሪያ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ማህበረሰብ አቀፍ የደንብ መተላለፍን የሚከላከል የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

!. በትምህርት ቤቶች የደንብ መተላለፍን የሚከላከል ክበባትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ክበባት እንዲቋቋሙ ወይም በተቋቋሙ ክበባት ላይ ግንዛቤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

!1.የደንብ መተላለፍን ለመከላከል የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ለእርምጃ አወሳሰድ ለቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ምክትል ስራ አስኪያጅ ያስተላልፋል፤

!2. በዋና ሥራአስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

4. Lead and coordinate the directorates under him; evaluate the thereof according to the relevant procedures of the city government; provide recognition upon approval;
5. Design methods that help to establish a system which enables to prevent code violations; follow up the implementation of the thereof;
6. Coordinate the provision of training for newly hired, assigned, or in-service paramilitary employees; implement same;
7. Give or cause the provision of training for governmental and non-governmental organizations regarding code violations;
8. Follow up, control, and coordinate the provision of awareness creation activities for the community about code violation actions through print and electronic media as well as face-to-face training;
9. Establish a system to prevent code violations through community-based initiatives by designing various mechanisms to enable the residents of the city to contribute their share in the prevention of code violations;
10. Cause the establishment of clubs in schools that prevent code violations in consultation with the concerned organs or cause the provision of awareness creations activities in already formed clubs;
11. Gather information that enables to prevent of code violations; transfer same to the measure-taking, controlling, and measure-taking deputy manager;
12. Carry out other activities that are specifically delegated to him by the general manager.

**!. <u>የክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1 በስሩ የሚገኙ የስራ አስተባባሪዎችን፣ ቡድኖች እና ባለሙያዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

2 የደንብ መተላለፎችን ይከላከላል፣ እርምጃ የመውሰድ ሥራዎችን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

3 ከደንብ ማስከበር ጋር በተያያዘ የወጡ አዋጆችን፤ ደንቦችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

4 የወረዳው ጽህፈት ቤትን ይደግፋል፤ ይከታተላል፤ አመራር ይሰጣል፤

5 የደንብ መተላለፍን ድርጊቶችን በተቀናጀ አኳኋን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚመለከታቸውን አካላት እና የክፍለ ከተማውን ነዋሪ በማሳተፍ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤

6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስሩ ያሉትን ፓራሚሊተሪ ሠራተኞች በክፍለ ከተማው ወይም በወረዳው ጽህፈት ቤት ውስጥ ባሉ የስራ መደቦች በጊዜያዊነት በመመደብ ወይም በማዘዋወር ሊያሰራ ይችላል፤

7 የፓራሚሊተሪውን፣ የባለሙያዉን፣ የአመራሩን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተገቢውን ሥልጠናና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

8 ግብረ ኃይል ያደራጃል፣ ኦፕሬሽን ሥራዎችን ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

9 እስከ ወረዳ ያሉ አጠቃላይ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ፤ እንዲደራጁና ለአስፈላጊው ጥቅም እንዲውሉ ያደርጋል፤

**10. <u>Duties and Responsibilities of the Office of the Sub-city</u>**

The Sub-city office shall have the following specific duties and responsibilities:

1. Coordinate and lead coordinators, teams, and experts under his supervision;
2. Prevent code violations; support, followup, and control measure-taking activities;
3. Ensure that proclamations, regulations, and directives in connection with code violations are implemented;
4. Support and follow up the office of the woreda; give leadership;
5. Work in coordination and collaboration through participating the concerned organs and residents of the sub-city to prevent and control code violation actions in an integrated manner;
6. If it deems necessary, may temporarily assign or transfer paramilitary employees to positions that are found in the offices of the sub-city or woreda;
7. Devise mechanisms that enable to enhance the capacity of the paramilitary, experts, and leaders; make sure that they obtain the relevant training and support;
8. Set up task force; lead and coordinate operations and follow up the implementation of the thereof;
9. Cause the gathering, organization, and proper utilization 2926 mprehensive information up to the woreda level;

!. በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለማስፈጸም ማስረጃዎችን በማደራጀት፣ ለክፍለ ከተማ ፍትህ ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፤ የቀረቡ ክሶችን አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

!1. ከሶስተኛ ወገን ጋር ለሚኖር ግንኙነት የክፍለ ከተማውን ደንብ ማስከበር ይወክላል፤

!2. ከደንብ ተላላፊዎች የሚወሰዱ ንብረቶችን እና ከአስተዳደራዊ ቅጣት የሚሰበሰቡ ገንዘቦች በፋይናንስ አሰራር ሥርዓት መሰረት እንዲፈጸም ያደርጋል፤

!3 በጨረታ ከሚሸጡ ንብረቶች የሚገኘውን ገንዘብ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ለክፍለ ከተማው ፋይናንስ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

!4. እጩ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰሮችን የክፍለ ከተማውን ነዋሪ በማሳተፍ ይመለምላል፤ የማስተቸት ሥራዎችን ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

!5. የፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን የዲሲፕሊን ጉዳዮች የሚያይ ኮሚቴ ያዋቅራል፤ ይከታተላል፤ ውሳኔ ይሰጣል፣

!6. ከወረዳው ከደንብ ተላላፊዎች የሚቀርበውን የይግባኝ ቅሬታ ውሳኔ ይሰጣል፤

!7. ከባለስልጣኑ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## !1. <u>የወረዳው ጽህፈት ቤት ተግባራትና ኃላፊነት</u>

የወረዳው ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1 በስሩ የሚገኙ የስራ አስተባባሪዎችን፣ ቡድኖች፣ ባለሙያዎችን እና የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

10. Organize evidence to execute the administration penalties of cases that were lodged to courts at every level and submit same to the justice office of the sub-city; follow up the execution of submitted lawsuits;
11. Represent the code enforcement office of the sub-city in its dealings with third parties;
12. Make sure that forfeited properties of transgressors and fees collected from administrative penalties are handled according to the financial procedures;
13. Follow up and control that the income obtained from the auctioned properties is transferred to the sub-city finance as per the law;
14. Enlist recruit paramilitary officers by participating in the residents of the sub-city; support and follow up the evaluation activities of the thereof;
15. Establish a committee that examines the disciplinary issues of paramilitary officers; follow up same and make decisions;
16. Make decisions on appeals submitted by transgressors that are found in the woredas;
17. Carry out other activities given by the authority.

## 11. <u>Duties and Responsibilities of the Office of the Woreda</u>

The woreda office shall have the following duties and responsibilities:

1. Coordinate and lead coordinators, teams, experts, and paramilitary officers under his supervision;

2 በአዋጅ ለባለስልጣኑ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባር መሠረት የደንብ መተላለፍ ድርጊትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ የኦፕሬሽን ሥራን ይመራል፤ ያስተባብራል፤

3 ከደንብ ማስከበር ጋር በተያያዘ የወጡ አዋጆችን፤ ደንቦችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ነዋሪው ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስሩ ያሉትን ፓራሚሊተሪ ሠራተኞች በወረዳው ውስጥ ባሉ የስራ መደቦች፣ ቀጠናና ብሎኮች በጊዜያዊነት በመመደብ ወይም በማዘዋወር ሊያሰራ ይችላል፤

5 ለማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚቀርቡትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለማስወሰን ማስረጃዎችን እንዲደራጁ በማድረግ ለክፍለ ከተማ ፍትህ ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6 ከደንብ ተላላፊዎች የተወረሱ የማይበላሹ ንብረቶችን በዓይነት በመለየት ለክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል፤

7 ከደንብ ተላላፊዎች የተወረሱ የሚበላሹ ንብረቶችን በተዋቀረው ኮሚቴ በየእለቱ እንዲሸጡ ያደርጋል፤ የሽያጭ ገንዘቡ በአግባቡ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፤

8 ከደንብ ተላላፊዎች የቅጣት ገንዘብ በመሰብሰብ ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት ለወረዳው ፋይናንስ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

9 እጩ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰሮችን የወረዳውን ነዋሪ በማሳተፍ የመመልመል፤የማስተቸት ተግባራትን ያከናውናል፤

2. Prevent and control code violation actions according to the power and duties entrusted to the authority as per the proclamation; take or cause the taking of measures; lead and coordinate operations;
3. Ensure that proclamations, regulations, and directives in connection with code violations are implemented; make sure that residents are aware of it using various media outlets;
4. If it deems necessary, may temporarily assign or transfer paramilitary employees to positions that are found in the office of the woreda, zones, and blocks;
5. Organize the evidence to execute the administration penalties of cases that were lodged to social courts and submit same to the justice office of the sub-city; follow up the execution of submitted lawsuits;
6. Identify the non-perishable forfeited properties of transgressors in kind and submit same to the store of the sub-city's office;
7. Cause the sale of the perishable forfeited properties of transgressors daily through the established committee; follow up that the income is deposited properly;
8. Collect fines levied on transgressors and control and follow up the submittal of same to the woreda finance according to the law;
9. Enlist recruit paramilitary officers by participating the residents of the woreda; cause the evaluation of same;

! የደንብ ማስከበር በጎ ፍቃደኞችንና ባለድርሻ አካትን በማቀናጀት ህብረተሰቡ በቅድመ መከላከል ሥራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

!1. ጽህፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገን ጋር ለሚኖር ግንኙነት የወረዳውን ጽህፈት ቤት ይወክላል፤

!2 የፓራሚሊተሪ ኦፊሰሮችን የቀላል ዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ በከባድ ዲሲፕሊን የሚታዩትን ክስ በመመስረት ለክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

!3. ከደንብ ተላላፊዎች የሚቀርበውን ቅሬታ አግባብ ባላው ሕግ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

!4. ከባለሥልጣኑ እና ከክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ሕገወጥ ንብረት ስለመያዝ፣ አሻሻጥና አወጋገድ</u>

### !2. <u>ሕገ-ወጥ ንብረትን ስለመያዝ</u>

1 ይህንን ደንብ በመተላለፍ በመንገድ ላይ ሕገወጥ ንግድ ሲካሄድበት የተገኘ ሸቀጥ ወይም የመንግስት መሬትን በመውረር በህ-ገወጥ መንገድ በተገነባ ግንባታ ላይ ያረፉ የግንባታ ቁሶችን ይይዛል፤

2 በህገወጥ የበረንዳ ንግድ፤ በህገ-ወጥ መንገድ በጎዳና ላይ ንግድ ወይም ለሌላ ማንኛውም ተግባር ተሰማርቶ ለሚገኝ ሰው በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ካልተነሳ ይይዛል፤

10. Coordinate code enforcement volunteers and stakeholders to ensure the participation of the commission in the pre-prevention activities;
11. Represent the office of the woreda in its dealings with third parties;
12. Make decisions on simple disciplinary cases on paramilitary officers; instigate charges on grave disciplinary cases and transfer same to the justice office of the sub-city; follow up the progress of same;
13. Make decisions on complaints submitted by transgressors according to the relevant laws;
14. Carry out other activities given by the authority and the office of the sub-city.

## <u>Part Three</u>

## <u>Confiscation of Illegal Properties, Selling, and Disposal</u>

### 12. <u>Confiscation of Illegal Properties</u>

1. Goods obtained from illegal street vending or construction inputs that are used for illegal construction through land grabbing by violating this Regulation shall be confiscated;
2. The properties of any person who is engaged in veranda business, illegal street vending, or any other activities shall be confiscated if he fails to remove the properties as per the issued notice;

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ንብረቱን የሚያነሳ አካል ያልተገኘ እንደሆነ የክፍለ ከተማው ወይም የወረዳው ጽህፈት ቤት ንብረቱን አስነስቶ ወደ ደንብ ማስከበር ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል፡፡ በተያዘው ንብረት ላይ አቤቱታ ሲቀርብ ጽህፈት ቤቱ ያወጣዉን ወጪ እና ኪሳራ ከደንብ ተላላፊዉ የአስተዳደራዊ ቅጣት ማስፈጸሚያ አቤቱታ ጋር አጣምሮ ለሚመለከተው የፍትህ አካል በማቅረብ ማስወሰን አለበት፡፡

**!3. ስለተያዘ ሕገ-ወጥ ንብረት አያያዝ**

1 የደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር ይህን ደንብ በመተላለፍ የያዘውን ንብረት ለወረዳው የደንብ ማስከበር ግምጃ ቤት ያስረክባል፣

2 የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳው ጽህፈት ቤት የተያዘውን ንብረት እንደ ንብረቱ ልዩ ባህሪ በአግባቡ ይይዛል፤ መያዙን ያረጋግጣል፣

3 በግብረ ኃይል የተያዙ ንብረቶች በክፍለ ከተማው ባለው የደንብ ማስከበር ግምጃ ቤት ገቢ ይደረጋል፤

4 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የተወረሰው ንብረት የሚበላሽ ከሆነ ንብረቱ እስኪሸጥ ድረስ በወረዳው እጅ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

3. Without prejudice to Sub-Article (1) and (2) of this Article, if no one removes the properties, the office of the sub-city or woreda shall clear the properties and submit it to the store of the code enforcement; if a complaint is lodged against the forfeited property, the office shall submit the expenses and loss incurred on it as well as a complaint for the execution of an administrative penalty on the transgressor to the relevant justice organ and ensure that a decision is made.

**13. Handling of Confiscated Illegal Properties**

1. The code violation follow-up, control, and measure-taking officer shall hand over the property seized in violation of this regulation to the store of the woreda's office;
2. The office of the sub-city or woreda shall hold the forfeited property properly based on the nature of the property; make sure that such is carried out;
3. Properties that are seized by the task force shall be handed over to the code enforcement store of the sub-city;
4. Notwithstanding to Sub-Article (1) of this Article, if the confiscated property is a perishable one, it shall remain under the possession of the woreda until it is sold.

**!4. ስለተያዙ ሕገ-ወጥ ንብረት አሻሻጥ እና አወጋገድ**

1 በዚህ ደንብ መሠረት የተያዘ ሕገወጥ ንብረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በባለሥልጣኑ ወይም በጽህፈት ቤት በጨረታ ይሸጣል፤ ሆኖም የተያዘው ሕገወጥ ንብረት የሚበላሽ ከሆነ የጨረታ ሂደቱን ሳይጠብቅ ንብረቱ የሚገኝበት ወረዳ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመው ኮሚቴ ወዲያውኑ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በጨረታ ሊሸጥ የማይችል እና ሊወገድ የሚገባ ንብረት በከተማ አስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር እና አያያዝ መመሪያ መሠረት ንብረቱ ይወገዳል፤

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከጨረታ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ድርጊቱ የተፈጸመበት ጽህፈት ቤት አማካኝነት በየደረጃው ለሚገኝ ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ገቢ መደረግ አለበት፤

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተያዘው ንብረቶች ሽያጭ እና ከአስተዳደራዊ ቅጣት ከሚሰበሰበው ገቢ ውስጥ ፷% ባለስልጣኑ ለአፍራሽ ግብረ ኃይል ኮንትራት ክፍያዎች፤ ለህገወጥ ግንባታዎች ማፍረሻ የተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ ክፍያዎች እና ለሌሎች ለእርምጃ አወሳሰድ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ለመሸፈን ሲውል ፵% ወደ አስተዳደሩ ፋይናንስ ፈሰስ ይደረጋል፤ አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፤

**14. Selling and Disposal of Confiscated Illegal Properties**

1. Illegal properties that were confiscated as per this law shall be sold through auction by the authority or the office as deemed necessary. However, if the forfeited properties are perishable, the woreda where the properties are found shall cause the immediate sale of the properties through the established committee without following the auction procedure;

2. A property that could not be sold as per Sub-Article (1) of this Article and that should be disposed according to the procurement and property administration and management of the city administration;

3. An income secured from the auction as per Sub-Article (1) of this Article shall be transferred to the finance office at every level by the code enforcement office where the action occurred according to the finance procedures of the city government;

4. Without prejudice to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, out of the income collected from the sale of properties and administrative fines, 60% of it shall be used to cover the expenses of the authority for contract payments for demolishing task force, vehicles and machinery used for demolishing illegal constructions and other necessary payments for taking measures and 40% of it shall be transferred to the finance of the city government; the implementation shall be specified through directive;

5 በዚህ ደንብ መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የሚቋቋመው ኮሚቴ በአስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፤

6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ ከደንብ ተላላፊዎች የተወረሱ ንብረቶችን እንዲለዩ በማድረግ በአስተዳደሩ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት ለሌላ ሰው በመስጠት ማስወገድ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለአስተዳደራዊ ቅጣት፣ እርምጃ አወሳሰድ እና አቤቱታ አቀራረብ

### !5. ስለአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ

1 በወንጀል ሕግ እና በሌሎች ሕጎች የተመለከተው የወንጀል ወይም የደንብ መተላለፍ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ በተላለፈ ማንኛውንም ሰው ላይ፡-

ሀ) እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ እና የማስነሳት እርምጃ ይወስዳል፤

ለ) ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

2 በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ደንብ የተላለፈ ሰው በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት የወረዳው ጽህፈት ቤት ቀርቦ በሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ ቅጣቱን ገቢ ማድረግ አለበት፤

5. The committee to be established for the disposal of confiscated properties as per this Regulation shall be carried out according to the procurement and property administration law of the city government;

6. If it deems necessary, the authority shall cause the identification of the confiscated properties and give the same to another person for disposal according to the procurement and property administration law of the city government.

## Part Four

## Administrative Penalties, Measure Taking, and Complaint Submittal

### 15. Taking Administrative Measures

1. Without prejudice to the penal code or code violation penalties stipulated under the penal code and other laws, the authority shall take the following measures on any individual:
   A. take measures of stopping the action, closing, sealing, and removal according to the nature of the offense;
   B. fine administrative penalties according to the schedule annexed with this regulation or other relevant laws
2. Any transgressor who is requested to pay an administrative penalty as per this regulation should bear the notice issued by the code violation follow-up, control, and measure-taking officer and appear in person at the woreda office where the offense was committed and pay the administrative penalty within three consecutive working days;

3 የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ መተላለፍ በተፈጸመበት ቦታ ቋሚ አድራሻ የሌላቸው ደንብ ተላላፊዎችን በደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የቅጣት ገንዘቡን ከፖሊስ ጋር በመሆን እንዲከፍሉ ያደርጋል፤

4 የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት መቀጮውን ገቢ ለማድረግ ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በቅጣት ሰንጠረዥ የተቀመጠዉን የመቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብበት ይደረጋል፡፡

**!6. ስለተደጋጋሚ ጥፋትና አስተዳደራዊ ቅጣት**

ማንኛውም ደንብ ተላላፊ የተወሰነበትን ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ የፈፀመ እንደሆነ፡-

1 በመጀመሪያ ደንብ መተላለፍ በቅጣት ሰንጠረዥ የተገለጸውን አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ እንዲከፈል ይደረጋል፤

2 ለሁለተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ደንብ መተላለፍ የፈጸመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተገለጸውን የገንዘብ መቀጮ እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

3. Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the code violation follow-up, controlling, and measure-taking officer, together with the police, shall ensure that transgressors who don't have a permanent address pay the fine;

4. If a transgressor is not willing to accept the penalty notice, such shall be perceived as receiving the notice and the penalty shall be carried out according to the provision of Sub-Article (6) of this Article;

5. If a person did not pay the administrative fine as per Sub-Article (2) of thisArticle, he shall be requested to pay double the imposed fine;

6. If a person is unable or unwilling to pay the fine according to Sub-Article (5) of this Article, he will be charged to appear before the relevant court and forced to pay double the amount of the fine specified under the penalty schedule.

**16. Recurrent Offences and Administrative Penalties**

If any transgressor commits similar code violations starting from the day he has paid the imposed fine in full or partially, he shall be forced to pay;

1. the administrative fine indicated under the penalty schedule for the first code violation;
2. double of the fine indicated under Sub-Article (1) of this Article for committing a similar code violation for the second time;

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ክፍያውን ካልፈጸመ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት ክፍያውን እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

**!7. ቅጣትን ስለማስፈፀም**

1 የወረዳው ጽህፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ !5 ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት ተገቢው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት አስተዳደራዊ መቀጮውን ገቢ ያላደረገን ወይም ያልፈጸመ ማንኛውም ደንብ ተላላፊ በደንቡ ላይ የተገለጸው አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲፈጸም ለሚመለከተው አካል ክስ እንዲመሰረትበት ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፤

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ክስ እንዲመሠረትበት የተደረገበት ደንብ ተላላፊ እንደአግባቡ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

**!8 ስለአቤቱታ አቀራረብ**

1 ይህንን ደንብ በመተላለፍ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው መከፈል ከሚገባው የመጨረሻው ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት የስራ ቀናት ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ ጽህፈት ቤት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፤

2 የወረዳ ጽህፈት ቤት የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ በ5 (በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣

3. if the person fails to pay the fine according to Sub-Article (1) and (2) of this Article, he will be charged to appear before the relevant court and forced to pay the thereof in collaboration with the relevant organ.

**17. Executing the Penalty**

1. The woreda office shall organize evidence and send it to the relevant organ for the prosecution of any transgressor who fails to pay or act accordingly after receiving the appropriate notice as per Sub-Article (2) of Article 15 of this regulation to execute the administrative penalty indicated in this regulation;
2. A transgressor who was prosecuted according to Sub-Article (1) of this Article shall appear before the relevant social court or another court with the proper authority for the execution of the penalty.

**18. Complaint Submittal**

1. Any person, to whom an administrative penalty has been imposed by violating this regulation, could lodge his complaint to the woreda office where the offense was committed within two working days after the due date for the payment of the fine;
2. The woreda office shall examine the submitted complaint concerning this regulation and other relevant laws and make decisions within 5 (five) working days;

3 አቤቱታው ተመርምሮ የተከፈለው ቅጣት አላግባብ መሆኑ ሲረጋገጥ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ ሥርዓት መሠረት የቅጣት ማስታወቂያው ተሰርዞ ለቅጣቱ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፤

4 የወረዳ ጽህፈት ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ለክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፤

5 ከክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ለባለስልጣኑ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፤

6 በባለስልጣኑ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የፓራሚሊተሪ ሠራተኞችና ኦፊሰሮች ተግባርና ኃላፊነት

### !9. የደንብ መተላለፍ ቅድመ መከላከል ኦፊሰሮች ተግባርና ኃላፊነት

1 በየቀጣናው የሚገኙ ህገ-ወጥ ተግባራት መረጃ በዓይነትና በብዛት በመለየት በዝርዝር ይይዛል፤

2 በነዋሪው ውስጥ የሚስተዋሉ የደንብ መተላለፎችን የግንዛቤ ክፍተት ይለያል፤

3 ከበጎ ፈቃደኞች ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት በየቀጣናው የደንብ መተላለፍን በጋራ የሚከላከሉበትን ስልት ይነድፋል፤ ሲፀድቅ ወደ ተግባር እንዲገባ ያደርጋል፤

3. Where it is proved upon investigation that the payment for the penalty was imposed inappropriately, the penalty notice shall be revoked and the fine payment shall be refunded in accordance with the financial procedures of the city administration;
4. Any person who is not satisfied with the final decision of the woreda office can submit his complaint to the sub-city office;
5. Any person who is not satisfied with the final decision of the sub-city office can submit his complaint to the authority;
6. Any person who is not satisfied with the final decision of the authority can submit his complaint to the relevant court.

## Part Five

## Duties and Responsibilities of Paramilitary Employees and Officers

### 19. Duties and Responsibilities of Code Violation Prevention Officers

1. Identify the type and number of occurrences of illegal activities in every zone and maintain the information in detail;
2. Identify the awareness gaps exhibited among residents regarding code violations;
3. Prepare a joint plan with volunteers and design a system to jointly prevent code violations in every zone; cause the implementation of same upon approval;

4 ለተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች በበራሪ ወረቀት፤ በመድረክ፤ ቤት ለቤት እና በመሳሰሉት ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

5 በትምህርት ቤቶች የቅድመ መከላከል ክበባትን በማቋቋም ወይም ከተቋቋሙ ክበባት ጋር በቅንጅት ህገ ወጥ ተግባራትን በጋራ የመከላከል ሥራ ይሰራል፤

6 ከቅድመ መከላከሉ ስራዎች በተጨማሪ ህገ ወጥ ተግባር ተፈጽሞ ሲገኝ ለቁጥጥር ኦፊሰሩ መረጃ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

**፳ <u>የሽፍት አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1 ሽፍት መሪዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል ፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤

2 ከሽፍት መሪዎች የሚመጣውን ሪፖርት ይቀበላል፤ ይጠምራል ለኃላፊው ሪፖርት ያቀርባል፤

3 የደንብ መተላለፍ ላይ ክትትል፣ቁጥጥር እና እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

4 በቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ የተሰሩ ስራዎችን መረጃ ያደራጃል፣

5 የውሎ ሪፖርት ይቀበላል ይገመግማል፤

6 ማንኛውም ሰው የፈፀመው የደንብ መተላለፍ በዚህ ደንብ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ከተገቢው ማስረጃ ጋር ጉዳዩን ለወረዳው ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፤

7 በቅርብ ኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

4. Ensure the creation of awareness for the various segments of society through fliers, formal meetings, door-to-door services, and similar other methods;
5. Carry out joint pre-prevention of illegal activities in a coordinated manner by establishing prevention clubs in schools or with that of the already established clubs;
6. Ensure that the control officer gets information regarding a committed illegal activity in addition to the prevention activities.

**20. <u>Duties and Responsibilities of the Shift Coordinator</u>**

1. Lead and coordinate shift leaders; give directions;
2. Receive and organize reports obtained from shift leaders; submit a report to the head;
3. Follow up and control code violations and cause the taking of measures; follow up the implementation of the thereof;
4. Organize the information on the activities done regarding controlling and measure-taking;
5. Receive daily reports and evaluate same;
6. If the code violation committed by any person entails a criminal liability in addition to the penalties to be imposed by this regulation, inform the case to the woreda office together with the relevantinformation;
7. Carry out other activities given by his immediate official.

**፳1.የሽፍት መሪ ተግባርና ኃላፊነት**

1 ለደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር ስምሪት ይሰጣል፤
2 የመስክ ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤
3 በደንብ መተላለፍ ድርጊቶች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
4 የውሎ ሪፖርት ይቀበላል፤ ይገመግማል፤
5 ለቅርብ ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤
6 ማንኛውም ሰው የፈፀመው የደንብ መተላለፍ በዚህ ደንብ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በማደራጀት ለቅርብ ኃላፊው ያሳውቃል፤
7 በቅርብ ኃላፊው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፳2 የደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር ተግባርና ኃላፊነት**

ማንኛውም የደንብ መተላለፍ፣ ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር ፡-

1 በዚህ ደንብና በሌሎች የደንብ መተላለፍን በሚመለከት በስራ ላይ ባሉ ደንቦች መሠረት ኦፊሰሩ በተመደበበት የሥራ ቦታና ጊዜ የደንብ መተላለፎችን የመለየት፣ የመከላከል፣ የመቆጣጠር፣ እርምጃ የመውሰድና የማስወሰድ ተግባር ያከናውናል፤

**21. Duties and Responsibilities of Shift Leader**

1. Deploy code violation follow-up,control, and measure-taking officers;
2. Supervise and monitor field activities;
3. Cause the taking of measures on code violation activities;
4. Receive daily reports and evaluate same;
5. Report activities to his immediate official;
6. If the code violation committed by any person entails a criminal liability in addition to the penalties to be imposed by this regulation, organize the relevant information and notify same to his immediate official;
7. Carry out other activities given by his immediate official.

**22. Duties and Responsibilities of the Code Violation Follow-up, Control, and Measure-Taking Officer**

Any code violation follow-up, control, and measure-taking officer shall:

1. Identify, prevent, and control code violations and take or cause the taking of measures against the thereof on his deployment areas and working hours based on this regulation and other active laws concerning code violations;

2 በየእለቱ የተሰሩ ስራዎችን በዕለት ሁኔታ መዝገብ ላይ ይመዘግባል፤

3 በዚህ ደንብ መሠረት የደንብ መተላለፍ ለፈፀመ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የቅጣት ማስታወቂያ ቅፅ በመሙላት ይሰጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ደንብ ተላላፊ በደንቡ መሠረት ገቢ ያላደረገውን መቀጮ ተፈጻሚ እንዲሆን ለወረዳው ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፣

5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የቅጣት ማስታወቂያ ቅፅ አልቀበልም ያለ ቋሚ አድራሻ ያለዉ ደንብ ተላላፊ ሲያጋጥም በ3 ቀን ጊዜ ዉስጥ መቀጮውን እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ በመኖሪያ ቤቱ ወይም በህገ-ወጥ ግንባታዉ ላይ በግልጽ ቦታ እንዲለጠፍ ያደርጋል፣ መቀጮውን ገቢ ያላደረገ እንደሆነ አስተዳደራዊ ቅጣቱ እንዲፈጸም ለወረዳው ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፣

6 የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ የደንብ መተላለፉ በተፈጸመበት ቦታ ቋሚ አድራሻ የሌለው ደንብ ተላላፊ ሲያጋጥም የደንብ መተላለፍ ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰር የቅጣት ገንዘብ እንዲከፈል ከፖሊስ ጋር በመተባበር ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

7 እንደ ደንብ መተላለፉ ሁኔታ በይዞታቸው ላይ ያለውን ንብረት ገቢ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ ጫት እንዲቅሙበት፣ ሽሻ እንዲያጨሱበት የሚያደርጉ፣ ግለሰቦችን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ ህገ-ወጥ ድርጊታቸዉን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማስነሳት፣ የማሸግ፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤ የተጣለባቸዉን መቀጮ ሲፈጽሙ የታሸገዉ እንዲነሳላቸዉ ያደርጋል፤

2. Register the daily activities on the daily record;

3. Fill and issue the appropriate penalty notice form for any individual that violates a code according to this regulation; follow up the execution of same;

4. Notify the woreda office for the execution of a penalty payment as per this regulation that was imposed on a transgressor who failed to pay the penalty according to Sub-Article (3) of this Article;

5. Upon encountering a transgressor who is unwilling to accept the penalty notice form as per Sub-Article (3) of this Article and has got a permanent address, post a notice on a visible place at his house or illegal construction site that warns to pay the fine within 3 days; if the transgressors fail to pay the fine, the officer shall notify same to the woreda code enforcement office for the execution of the administrative penalty;

6. Without prejudice to Sub-Article (5) of this Article, upon encountering a transgressor who does not have a permanent address in the place where the code violation was committed, the code violation follow-up, control, and measure-taking officer, together with the police, shall ensure that the transgressor pay the fine and such is executed;

7. As per the nature of the code violation, stop individuals or business entities from their illegal activities of using their properties under their title possession for chewing chat or smoking shisha for personal gains or to benefit others, close, remove, seal the thereof, and take or cause the taking of measures; cause the opening the shut down when they pay the imposed fine;

8 መንገድ ዘግተዉ የሚቆሙ መኪናዎች፣ ባልተፈቀደ ቦታ አፈር፣ አሸዋ ወይም የመሳሰሉ ቁሶችን በተሽከርካሪ የሚደፉ ደንብ ተላላፊዎች ከአካባቢው ትራፊክ ፖሊስ ጋር በጋራ በመሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ቦታና ሰዓት እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤

9 ማንኛዉም በፓራሚሊተሪ ሠራተኝነት የተቀጠረ ሰዉ 5 ዓመት የማገልገል ግዴታ አለበት፤

! በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተቀመጠዉን የአገልግሎት ጊዜ ሳያጠናቅቅ ከስራዉ የሚለቅ ለስልጠና የወጣውን የሥልጠና ወጪ መክፈል ይኖርበታል፤

!1 ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ደንብ አስከባሪነቱንና ማንነቱን የሚገልጽ የደረት ባጅ እንዲሁም ማዕረጉን ሊያሳይ የሚችል የማዕረግ ምልክት ከደንብ ልብሱ ጋር ማድረግ አለበት፤

!2 ሕገወጥ ግንባታ፣ ጫት ማስቃም፣ ሽሻ ማስጨስ መፈፀሙን ሲመለከት ወይም ጥቆማ ሲደርሰው እና አጣርቶ ትክክለኛነቱን ሲያረጋግጥ በዚህ ደንብ መሠረት ሕገወጥ ድርጊቱን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፤ ሆኖም ከህግ አግባብ ውጪ በሰው መብትና ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፤

!3 ማንኛውም ሰው የፈፀመው የደንብ መተላለፍ በዚህ ደንብ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ከተገቢው ማስረጃ ጋር ጉዳዩን ለወረዳው ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፣

!4 በወረዳው ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

8. Take or cause the taking of measures on transgressors that block roads using cars, dump soil, sand, or other similar materials on unauthorized sites using vehicles together with the traffic police officer around the area at the place and time where the action was committed;

9. Any person who is hired as a paramilitary employee shall be obliged to serve 5 years;

10. Any person who fails to serve the service period indicated under Sub-Article (9) of this Article and resigns should cover the training expenses;

11. Dress his uniform, put on a chest badge that indicates him as a code enforcement officer and his identity and clearly shows his rank when he is undertaking his job;

12. Shall have the obligation to prevent, control, and take the appropriate measure against illegal activities based on this regulation when he encounters or receive reports of illegal constructions, chat chewing, or shisha smoking activities after examining and confirming the accuracy of the thereof; however, he shall be held accountable for the damage he incurs on the rights and properties of individuals done in contravention of due process of law;

13. If the code violation committed by any person entails a criminal liability in addition to the penalties to be imposed by this regulation, inform the case to the woreda office together with the relevantinformation;

14. Carry out other activities given by the woreda office.

## ክፍል ስድስት

## የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ምልመላ፤ ቅጥር፤ ምደባ ፤ዝውውርና ድልድል

### ፳3 እጩ የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ምልመላና ሥልጠና

1 የእጩ ፓራሚሊተሪ ሠራተኞች የመመልመያ መስፈርት ባለስልጣኑ በሚያወጣው የመመዘኛ መስፈርት እና መመሪያ ይወሰናል፤

2 እጩ የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ምልመላ ለማስፈፀም ባለሥልጣኑ በየደረጃው አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

3 እጩ የፓራሚሊተሪ ሰራተኞች ሥነ-ምግባራቸው፣ የአካል ብቃታቸው እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመመልመያ መስፈርቶችን አሟልተዉ ሲገኙ ይመለመላሉ፤

4 በኮሚቴው የተመለመሉ ዕጩ የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ወደ ሥልጠና ከመግባታቸው በፊት በነዋሪው አስተያየት እንዲሰጥ ግልጽ በሆነ ቦታ ዝርዝራቸው ይለጠፋል፤

5 የተመለመሉ ዕጩ የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች፣ መሠረታዊ የወታደራዊ እና የንድፈ ሀሳብ ሥልጠና መውሰድና ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ለሥራው ይቀጠራሉ፡፡

## Part Six

## Recruitment, Employment, Assignment, Transfer, and Deployment of Paramilitary Employees

### 23. Recruitment and Training of Candidate Paramilitary Employees

1. The recruitment criteria for the candidate paramilitary employees shall be specified through an assessment requirement and directive to be issued by the authority;
2. The authority shall establish a committee composed of the relevant organs at every level for the recruitment of candidate paramilitary employees;
3. Candidate paramilitary employees shall be recruited when they meet the recruitment criteria through their ethical standards, physical fitness, and other relevant requirements;
4. The list of candidate paramilitary employees that were recruited by the committee shall be posted in a visible place to get comments from residents before they receive training;
5. The recruited paramilitary employees should take basic military and theoretical training and will be hired when they are only qualified for the job.

**፳4 ቃለ-መሐላ**

1 ማንኛውም የበለሥልጣኑ እጩ ፓራ ሚሊተሪ ሠራተኞች በከተማ አስተዳደሩ ክልል የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፎችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መሠረታዊ የወታደራዊ እና የንድፈ ሀሳብ ሥልጠና እንዳጠናቀቀ ስራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሐላ ይፈጽማል፡-

"እኔ ------------ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በደንብ ማስከበር ባለስልጣን ኦፊሰር ሆኜ ህዝብና መንግስት የጣለብኝን አደራ ለመወጣት፣ በእዉነትና በታማኝነት፣ ህዝብን ለማገልገል፣ በማንኛዉም ጊዜና በታ ህገ-መንግስቱንና የሀገሪቱን ህጎች ለማክበር፣ በስራዬ ምክንያት ያወቅሁትንና በሚስጥርነት መያዝ ያለበትን በመጠበቅ፣ የደንብ መተላለፍን የመከላከል፣ የመቆጣጠር፣ እርምጃ የመዉሰድና የማስወሰድ ተግባራትን ለመወጣት እና የመንግስት ፖሊሲዎችን ለመፈጸም እና ለማስፈፀም ቃል እገባለሁ"።

2 የተፃፈው ቃለ መሀላ በፓራሚሊተሪ ሠራተኛው ተፈርሞ በግል ማህደሩ ውስጥ ይቀመጣል።

**፳5. የቅጥር ዉል**

1 እጩ ፓራሚሊተሪ ሆኖ የተመለመለው ሰው የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰር የሚሆነው የደንብ ማስከበር መሠረታዊ የወታደራዊ እና የንድፈ ሀሳብ ስልጠና አጠናቆና ቃለመሀላ ፈጽሞ የቅጥር ውል ከፈረመ በኋላ ነዉ፤

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ዘመን የሚታሰበዉ ስልጠና አጠናቆና ቃለመሀላ ፈጽሞ የቅጥር ውል ከፈረመ በኃላ ነው።

**24. Oath**

1. Any candidate paramilitary employee of the authority shall, after finishing the basic military and theoretical training that enables him to prevent, control, and take measures against code violations that are committed within the vicinity of the city administration, take the following oath before the commencement of his work:

   *"I ------------------------------ being an officer at the Addis Ababa city government code enforcement authority solemnly swear to sincerely, faithfully, and ethically serve the people and the government, and to respect the constitution and the laws of the country at all times and conditions, and not to disclose any information that I am aware of by reasons of my duties and classified as confidential, and to undertake the responsibilities to prevent, control, take or cause the taking of measures against code violations, and execute or cause the execution of government policies."*

2. The written oath shall be signed by the paramilitary employee and kept in his file.

**25. Employment Contract**

1. A candidate paramilitary shall be regarded as a paramilitary officer after he has completed the basic code enforcement military and theoretical training and taken an oath and entered into an employment contract and signed the thereof;
2. The service period shall be calculated after the office has completed the training and took the oath and signed the employment contract.

**፳6 በዝዉዉር ወይም በተጠባባቂነት ስለማሰራት**

1 ባለስልጣኑ ለስራዉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ማንኛዉንም የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰር ከአንድ የስራ መደብ እኩል የስራ ደረጃና ደሞዝ ወዳለዉ ሌላ ተመሳሳይ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሰራ ይችላል፣

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ ቢኖርም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ባለስልጣኑ የአንድን የፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰር ደሞዝ ሳይጨምር ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ በተከታታይ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ በተጠባባቂነት ወይም በውክልና መድቦ ማሰራት ይችላል፤

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገዉ ቢኖርም ባለስልጣኑ ከስድስት ወር ለበለጠ ጊዜ በተጠባባቂነት ወይም በዉክልና ተመድቦ የሠራ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር ደረጃዉ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅማጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ ይችላል፡፡

**፳7 በመደበኛ ስራ ላይ ወይም ከመደበኛ ስራ ውጭ ሆኖ ስለሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና**

1 ማንኛውም የፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰር ለተመደበበት ሥራ ብቁ የሚያደርግ በመደበኛ ሥራ ላይ ወይም ከመደበኛ ሥራ ዉጭ ሆኖ የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፤

2 ባለስልጣኑ ከፓራሚሊተሪ ኦፊሰሩ ጋር ከተስማማ በሚፈልገው የሙያ ወይም የሥራ መደብ ላይ አሰልጥኖ ይመድባል፤ መብትና ግዴታቸው በውሉ መሰረት ይፈጸማል፡፡

**26. Transfer or Acting Assignment**

1. The authority may, if it deems necessary for the work, transfer a paramilitary officer from one position to another similar position with equal grade and salary or from one place of work to another;
2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, where circumstances do require the authority may assign a paramilitary officer, without salary increment, to a higher position in an acting capacity or through delegation for not more than six months consecutively;
3. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the authority may allow the entitlement of the benefits for the position if the paramilitary officer is assigned in an acting capacity or through delegation for more than six months.

**27. Provision of Education and Training on-duty and off-duty Basis**

1. Any paramilitary officer shall be required to involve in an on-duty or off-duty education and training that enables him to build his capacity for the job he is assigned to;
2. The authority may train and assign a paramilitary officer in a given profession or position of its choice upon their mutual consent; their rights and obligations shall be entertained as per the concluded contract.

**፳8 ድልድል**

1 ባለስልጣኑ አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰሩን አወዳድሮ ባለው ክፍት የስራ መደብ ደልድሎ ማሰራት ይችላል፤

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሩ ሥራውን ሲያከናውን በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ተልዕኮውን መፈጸም የማይችልበት ሁኔታ ሲገኝና በባለሥልጣኑ ውስጥ ባሉ ሌሎች ክፍት የፓራሚሊተሪ የሥራ መደቦች ላይ የተቀመጠውን መመዘኛ የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ይደለደላል፣

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚደለደል የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰር ቀደም ሲል ይዞት በነበረው ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ የነበረው ደመወዙና ጥቅሞቹ አይቀነስበትም።

**ክፍል ሰባት**

**የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች ደመወዝ፣ የሥራ ሰዓት እና ፍቃድ**

**፳9 ስለደመወዝ ደረጃ እና ጥቅማጥቅም**

1 ፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ለተመደበበት የሥራ ክፍል የተወሰነዉን ደሞዝና ጥቅማጥቅም ያገኛል፣

2 ባለሥልጣኑ በከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ መደቦች ምዘና፣ ደረጃዎች ምደባና የደመወዝ ስኬል ደንብ መሠረት የአስተዳደሩን የፋይናንስ አቅም ያገናዘበ ለፓራሚሊተሪ ሠራተኞች የሚያገለግል የደመወዝ ደረጃ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር አጥንቶ ለካቢኔው ያቀርባል፤ በካቢኔው ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**28. Redeployment**

1. The authority may redeploy a paramilitary officer to a vacant position based on competition when it studied a new organizational structure and implement the thereof;
2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a paramilitary officer shall be redeployed if he is unable to undertake his mission due to the injury he sustained while he is on duty and if he meets the set requirements for the other vacant paramilitary positions in the authority;
3. A paramilitary officer who is redeployed according to Sub-Article (2) of this Article, his salary and benefits that he gets due to his prior grade and service period will not be deducted.

**Part Seven**

**Salary, Working Hours, and Leave of Paramilitary Employees**

**29. Salary and Benefits**

1. A paramilitary officer shall get the specified salary and benefits for the department he has been assigned to;
2. The authority shall, in collaboration with the relevant executive organs, study a salary scale for the paramilitary employees according to the civil servants' job position evaluation, grading, and salary scale regulation of the city government and taking the financial capacity of the administration into consideration and submit same to the cabinet; implement same upon its approval by the cabinet;

3 ባለሥልጣኑ የፓራሚሊተሪ ሠራተኞችን የአበልና የጥቅማጥቅም ዓይነቶችና መጠን ጥናት በማድረግና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ለካቢኔው ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4 ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት ተፈላጊ ችሎታና መመዘኛ የሚጠይቅ እኩል ደረጃ ያላቸው ሥራዎች እኩል መነሻ ደመወዝ ይኖራቸዋል፤

5 የሥራ አፈጻጸም ምዘና ዉጤቱ አጥጋቢ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ፓራሚሊተሪ ሠራተኛ የደሞዝ ጭማሪ ያገኛል፤

6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው የደመወዝ ጭማሪ በተመለከተ በመንግስት ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ደንብና መመሪያ መሠረት በሚወሰነው ጊዜ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**፴ <u>መደበኛ የስራ ሰዓት</u>**

1 የፓራ ሚሊተሪ ሠራተኛ መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደየሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳምንት ከ፴9 ሰዓት መብለጥ የለበትም፤

2 በፓራ ሚሊተሪ የሥራ መደብ ላይ የሚሰሩ ኦፊሰሮች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. The authority shall, in consultation with the relevant organs, study the types and amount of allowance and benefits of paramilitary employees and submit same to the cabinet; implement same upon approval;
4. Jobs that have equal grades and that demand similar or the same qualification and requirements shall have an equal base salary;
5. A paramilitary employee having a satisfactory or above that job performance evaluation result shall be entitled to a salary increase;
6. The salary increment that was provided under Sub-Article (5) of this Article shall be implemented according to the specified period under the civil servants' salary increment regulation anddirective.

**30. <u>Regular Working Hours</u>**

1. The regular working hours of a paramilitary employee shall be determined based on the condition of the work and it should not exceed 39 hours a week;
2. The time when the office hours of the officers that are engaged in the paramilitary positions begin and end shall be determined through a directive to be issued by the authority.

## ፴1 ስለትርፍ ሰዓት ሥራ

1 የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሰራ ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር የማካካሻ እረፍት ወይም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ይሰጠዋል፤
2 የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር በትርፍ ሰዓት ስራ የሚፈጸሙ ተግባራት የሚታዘዙበት ሁኔታ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
3 ትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፣ ስለክፍያው መጠንና የማካካሻ ዕረፍት የሚሰጥበት ሁኔታ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ባወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤
4 መደበኛ የዕለት ሥራን ለመጨረስ የሚደረግ ሥራ እንደ ትርፍ ሰዓት ሥራ አይቆጠርም።

## ፴2 ስለ ሕዝብ በዓል ቀናት

1 ማንኛውም በባለስልጣኑ ውስጥ በፓራሚሊተሪ የስራ መደብ ላይ የሚሰራ ሠራተኛ በህዝብ በአላት ወይም በመንግስት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን የመደበኛ ስራውን ማከናወን ይኖርበታል፤
2 በፓራ-ሚሊተሪ ሥራ መደብ ላይ የሚሰራ ኦፊሰር በህዝብ በዓላት ወይም በመንግስት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን ሠራተኛው የማካካሻ እረፍት ወይም የትርፍ ሰአት ክፍያ የሚሰጠው ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ከሰራ ነው፤
3 በፓራ-ሚሊተሪ ኦፊሰር የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በገንዘብ ሲለወጥ የኦፊሰሩ የአንድ ቀን ደመወዝ የሚታሰበው ያልተጣራ የወር ደመወዙን በ፴ ቀናት በማካፈል ነው።

## 31. Overtime Work

1. Any paramilitary employee who has worked overtime is entitled to a compensatory leave or overtime pay;
2. The conditions to carry out overtime activities by the paramilitary employee shall be specified through a directive to be issued by the authority;
3. The conditions to permit overtime work, the amount of payment, and the conditions to allow the compensatory leave shall be determined by the directive issued by the public service and human resource development bureau;
4. Work that is done to finish the regular daily activities shall not be regarded as overtime work.

## 32. About Public Holidays

1. Any employee who is working in a paramilitary position in the authority should carry out his regular duties on public holidays or on a day that offices are closed by the order of the government;
2. An officer who is working in a paramilitary position will get a compensatory leave or overtime pay if he works extra time beyond the regular working hours on public holidays or on a day that offices are closed by the order of the government;
3. Where payment is made to a paramilitary officer instead of his annual leave, the daily salary of the officer shall be calculated by dividing the gross monthly salary by 30 days.

**፴3 የህግ ማዕቀፍ ወይም የህግ ድጋፍ አገልግሎት**

የፓራሚሊተሪ ሠራተኞች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሚወጡበት ጊዜ ብቻ ለሚደርስባቸው የህግ ክርክር ወይም ክስ ተቋሙ ጠበቃ በማቆም ለፓራሚሊተሪ ሠራተኛው ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮች ግዴታ እና ሥነ-ምግባር፣**

**፴4 የፓራ ሚሊተሪ ኦፊሰሮች ግዴታና ሥነ-ምግባር በተመለከተ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር ፶6/2ሺ! አንቀጽ ፷6 የተደነገገው ግዴታና የሥነ-ምግባር መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ግዴታና ሥነ-ምግባር የመከተል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**፴5 የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ መሰረታዊ ግዴታዎች**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ፡-

1 የመንግስትን ፖሊሲ፣ የባለሥልጣኑን ደንብ፣ መመሪያዎችና የአሰራር ሥርዓቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፤
2 መላ ጉልበቱንና ችሎታውን ለሕዝብ አገልግሎት ማዋል አለበት፤
3 በሥራ መዘርዝሩ ላይ የተሰጡትን ተግባሮችና ሌሎች በሕጋዊ መንገድ የሚሰጡ ትዕዛዞችን መፈፀም አለበት፤

**33. Legal Frameworks or Legal Support Service**

The authority shall provide a free legal support service for the paramilitary employees when they face a lawsuit or prosecution while they are only undertaking their entrusted responsibilities through hiring lawyers.

**Part Eight**

**Obligations and Ethics of Paramilitary Officers**

**34. Regarding the Obligations and Ethics of Paramilitary Officers**

Without prejudice to Article 66 of the Addis Ababa city government civil servants' proclamation number 56/2018, a paramilitary employee should adhere to the following stated obligations and ethical standards.

**35. Basic Responsibilities of a Paramilitary Employee**

Any paramilitary employee shall:

1. have the obligation to respect or cause the respect of government policies, the regulations, directives, and procedures of the authority;
2. devote all his capacity and ability for the public service;
3. carry out his duties specified under his job descriptions and other orders given to him as per the law;

4 ከኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ ምርመራ በስተቀር ከሥራው ጋር በተያያዘ በበቂ ምክንያት የሕክምና ምርመራ እንዲያደርግ በባለሥልጣኑ ሲጠይቅ ለምርመራ የመቅረብ ግዴታ አለበት፤

5 ለሥራ ጓዱና ለመሪው ታማኝና ግልፅ መሆን አለበት፤

6 በሥራ ላይ በጓዱ ላይ በአካሉ ወይም በህይወቱ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመከላከልና የመርዳት ግዴታ አለበት፤

7 ለዚህ ክፍል ድንጋጌዎችና ባለሥልጣኑ ለሚያወጣቸው ሌሎች የሥነ-ምግባር መመሪያዎች ተገዥ መሆን አለበት፡፡

**፴6 ታዛዥነት**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ፡-

1 ሥራውን ባለው ዕውቀትና ችሎታ መሉ ለሙሉ በመጠቀም መፈፀም፤

2 የተመደበበትን መደበኛ ሥራና ሌላውንም ተመሳሳይ ህጋዊ ትዕዛዝ መፈፀም አለበት፤

3 የበላይ የኃላፊውን ትዕዛዝ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

**፴7 ሚስጥር መጠበቅ**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ አግባብነት ባለው ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገርንና የህዝብን ደህንነት የሚጎዱ በመሆናቸው ሚስጥር የተባሉ መረጃዎችን፣ ሥልጣን ባለው ኃላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ ወይም በሥራ ላይም ሆነ ከስራ ውጪ ጉዳዩን እንዲያውቀው የሚገባው ሰው ካልሆነ በቀር በአሰራር ሚስጥር የሆኑትን መረጃዎችን ለሌላ ማናቸውም ሰው መግለፅ የለበትም፡፡

4. have the obligation to take medical examination when requested by the authority in connection with his job having ample reasons to do so, except for HIV/AIDS testing;
5. be an honest and genuine officer for his colleagues and leader;
6. have the obligation to protect his colleagues from any physical harm or life threatening injuries while on duty and help them;
7. have the obligation to respect the provisions of this part and other ethical standards to be issued by the authority.

**36. Obedience**

Any paramilitary employee is obliged to:

1. carry out his work using all his knowledge and ability;
2. undertake his regular work he is assigned to and other similar lawful orders;
3. respect the order of his higher official.

**37. Confidentiality**

Without prejudice to the provisions promulgated under the relevant laws, any paramilitary employee should not disclose any information which is regarded as confidential as it harms the interest of the nation and the public for any other person unless he is properly ordered by an authorized official or to a person who needs to be aware of the matter either being on duty or off duty.

**፴8 ስለ ስጦታ**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ በሠራተኛነቱ ለሰጠው ወይም እንዲሰጥ ለሚጠበቀው አገልግሎት ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም፡፡

**፴9 ሌላ ስራ መስራት ስለሚከለከልበት ሁኔታ**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ለመስሪያ ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማናቸውም አኳኋን ከተመደበበት ስራ ጋር የሚቃረን ወይም ከፓራሚሊተሪ ሠራተኛነቱ ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም ሌላ ስራ መስራት የለበትም፡፡

**፵ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም**

1 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ለሥራ ማከናወኛ የተሰጡትን መሳሪያዎችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት፤

2 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ለሥራ ማከናወኛ የተሰጡትን መሳሪያዎችና መገልገያዎች ቆጥሮ የመረከብና የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፤

3 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ የሚገለገልባቸውን መሳሪያዎች ደህንነታቸውን የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ የማፅዳት ኃላፊነት አለበት፤

4 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ የወትሮ ዝግጁነቱን አረጋግጦ የመገኘት ኃላፊነት አለበት፡፡

**38. Regarding Gifts**

Any paramilitary employee should not request or accept any kind of gift for the service he provides or is expected to provide as an employee.

**39. Conditions that Prohibit to Engage in Other Work**

Any paramilitary employee should not engage in any other activity that compromises his service for the authority or creates a conflict with the duties he is assigned to or is incompatible with his status as a paramilitary employee.

**40. Handling and Use of Equipment**

1. Any paramilitary employee shall have the responsibility to properly use the material and equipment which are supplied to him to do his job;
2. Any paramilitary employee shall have the responsibility to enumerate and receive the material and equipment which are supplied to him to do his job and hand over the thereof;
3. Any paramilitary employee is responsible for the safety, care, and cleaning of the material he is using to do his job;
4. Any paramilitary employee shall be responsible to make himself ready at all times.

**፵1 በዕዳ የመጠየቅ ኃላፊነት**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ለስራ ማከናወኛ የተሰጡትን መሳሪያዎችና መገልገያዎች ላይ ለሚደርሱ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በኦፊሰሩ ቸልተኝነት ወይም ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው፡፡

**፵2 የደንብ የመልበስ ግዴታ**

1 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ በሥራ ላይ ሲሆን የደንብ ልብሱን አሟልቶ መልበስ ይኖርበታል፤

2 ባለሥልጣኑ የደንብ ልብስ እና የሥነ-ሥርዓት አከባበር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፵3 ንፅህና ስለመጠበቅ**

1 ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ የግል ንፅህናውን እና የደንብ ልብሱን ንፅህና በሚገባ መጠበቅ አለበት፡፡

2 ስለንፅህና አጠባበቅ በባለሥልጣኑ የሚወጡ መመሪያዎችን ማክበር አለበት፡፡

**፵4 የተከለከሉ ተግባራት**

ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ ፡-

1 የተሰጠውን የደንብና የሥራ ልብስ ለሌላው ሰው ማዋስ ወይም መሸጥ አይቻልም፡፡

2 ባለሥልጣኑ ሳይፈቅድ ማንኛውም ዓይነት የዕርዳታ መዋጮ ማሰባሰብ አይችልም፤

3 የደንብ ልብሱን ሲለብስ ጌጣጌጥ ማድረግ የለበትም፤ ሆኖም ባለትዳር ከሆነ የጋብቻ ቀለበትና ተላጣፊ የጆሮ ጌጥ ብቻ ማድረግ ይችላል፡፡

**41. Extent of Liability**

Any paramilitary employee shall be held liable for the damage or loss of the material or equipment at his disposal to do his job when it is confirmed that such has happened as a result of the negligence or ill intentions of the employee.

**42. Obligation to Wear Uniforms**

1. Any paramilitary employee should wear his uniform while he is on duty;
2. The authority shall issue a directive regarding uniform, and respecting procedures.

**43. Personal Hygiene**

1. Any paramilitary employee should maintain good personal hygiene and the neatness of his uniform;
2. Any paramilitary employee should comply with the neatness directive to be issued by the authority.

**44. Prohibited Activities**

Any paramilitary employee should:

1. not lend or sell his uniform to another person;
2. not collect money for any kind of support without the permission of the authority;
3. not wear jewellery while wearing his uniform. However, if he is married, he can have his wedding ring and only wear attached earrings.

**፵5 የኃይል አጠቃቀም**

1 የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት ኃላፊነቱን እንዳይወጣ የሚያደርግ ግልጽ ተቃውሞ ካጋጠመዉና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ባለሥልጣኑን በማሳወቅ ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፤

2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ሀይል መጠቀም የሚችለው፡-

ሀ) በራሱ ወይም በስራ ባልደረባ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል፣

ለ) የተወረሰ ንብረትን ከደንብ መተላለፍ እርምጃ አወሳሰድ ኦፊሰሩ ወይም ህገ-ወጡን ከሚቀለብሰው ግብረ-ሀይል በመንጠቅ ለማምለጥ የሚሞክረዉን፣ ንብረቱን ነጥቆ በመያዝ በማምለጥ ላይ ያለን ህገወጥ ድርጊት ፈጻሚ ለማስቆም ነው፤

ሐ) የሚጠቀመው ተመጣጣኝ ሀይል ኃላፊነቱን እንዳይወጣ የሚያደርገውን መሰናክል ለማስቀረት ብቻ መሆን አለበት፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተደነገገው ውጭ የኃይል እርምጃ የወሰደ ማንኛውም የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**ክፍል ዘጠኝ**

**የዲሲፕሊን እርምጃዎች፣ የቅሬታ አቀራረብ እና አገልግሎት ስለማቋረጥ**

**፵6 የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ**

የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ የፓራሚሊተሪ ሠራተኛው በፈፀመው የዲሲፕሊን ጉድለት ተፀፅቶ እንዲታረምና ብቁ ሠራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

**45. Use of Force**

1. A paramilitary officer may use reasonable force, by notifying the authority, when he encounters clear objections that inhibit him to carry out his responsibilities while he is on duty and when he has no alternative options;
2. According to Sub-Article (1) of this Article, he can use power to:

A. protect himself or his colleague from plausible injuries;

B. stop a transgressor who snatches the forfeited property from the code violation and measure-taking officer and run or from the task force that averts the illegal activity;

C. reasonable force should only be used to prevent the obstacles that inhibit him to carry out his responsibilities;

D. any paramilitary officer that uses force contrary to the provisions of this Sub-Article shall be held liable as per the relevant laws.

**Part Nine**

**Disciplinary Measures, Complaint Submittal, and Termination of Service**

**46. The Objective of a Disciplinary Penalty**

The objective of a disciplinary penalty is to ensure that a delinquent paramilitary employee is regretted and learned from his mistakes and help him to become a competent employee or dismiss him when he is found defiant.

**፵7 የዲሲፕሊን ቅጣት ዓይነቶችና አመዳደብ**

1 የዲሲፕሊን ጉድለት የፈፀመ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፣
   ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ ፣
   ለ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ፣
   ሐ) እስከ አራት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፣
   መ) እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ለሚደርስ ጊዜ በሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣
   ሠ) ከሥራ ማሰናበት፤

2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ለ) የተዘረዘሩት ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፤

3 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተራ ፊደል (ሐ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፤

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) መሠረት ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ በማድረግ የተቀጣ የፓራሚሊተሪ ኦፊሰር የቅጣት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ፡-
   ሀ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረ የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ ክፍት የሥራ መደብ ካለ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት፣
   ለ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት የነበረ የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ መደብ ካልተገኘ ክፍት የሥራ መደቡ በተገኘበት ጊዜ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት በሥራ መደቡ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፤

**47. Types and Classifications of Disciplinary Measures**

1. Depending on the gravity of the offense, any one of the following penalties may be imposed on an employee of the authority for disciplinary defects:
   A. oral warning;
   B. written warning;
   C. fine up to 4 months' salary;
   D. lowering of grade and salary up to a period of two years;
   E. dismissal.
2. The penalties specified under letter (A) to (B) of Sub-Article (1) of this Article shall be classified as simple disciplinary penalties;
3. The penalties specified under letter (C) to (E) of Sub-Article (1) of this Article shall be classified as rigorous disciplinary penalties;
4. A paramilitary officer who has been demoted in accordance with letter (D) of Sub-Article (1) of this Article shall be reinstated, upon the lapse of his period of punishment:
   A. when there is a similar vacant position is available, without any promotion procedure;
   B. in the absence of a similar vacant position, he shall be reinstated to a vacant position without any promotion procedure when it becomes available at a later time.

5 አንድ ሠራተኛ በዲሲኘሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይና ሊጠቀስበት የሚችለው፡-

ሀ) ቀላል የዲሲኘሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ፣

ለ) ከባድ የዲሲኘሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመት፣ ይሆናል፡፡

**፵8 ቀላል የዲሲፐሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች፤**

የሚከተሉት ጥፋቶች ቀላል የዲሲፐሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ናቸው፡-

1 የቅርብ የሥራ ኃላፊውን ፈቃድ ሳያገኝ ከሥራ መቅረት፤

2 በሥራ ሰዓት የግል ወይም የሌላ ሰው ሥራ መሥራት፤

3 የሥራ ባልደረባው የብቃት ማነስ ሳይኖርበት የብቃት ማነስ እንዳለበት አድርጎ በመጥፎ ልበና ማሳወቅ፤

4 የሥራ ባልደረባው ህገ ወጥ ወይም ብልሹ የሥነ-ምግባር ድርጊት ሲፈጽም ለሥራ ኃላፊው ወይም ለሚመለከተው ሌላ አካል አለማሳወቅ፤

5 ቅን ልበናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ ማቅረብ፤

6 ያለበቂ ምክንያት ጠቃሚ መረጃን ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች ወይም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሌሎች ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች አለመስጠት፣

7 ሕጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጁ የሚገኘውንና ለማንም ግልጽ እንዳይደረግ ያልተከለከለ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፤

5. After a disciplinary measure has been taken on an employee, such measure shall be referred to and remain as a record:

   A. for two years as of the day the penalty decision is made, where the penalty is a simple one;

   B. for five years as of the day, the penalty decision is made, where the penalty is a rigorous one.

**48. Offenses that Entail Simple Disciplinary Penalties**

The following offenses shall entail simple disciplinary penalties:

1. Absence from work without the permission of an immediate official;
2. Carry out personal activities or other's work during working hours;
3. Adversely inform as if his colleague is incompetent;
4. witnessing the illegal or unethical activities of his colleague;
5. Provide reports in bad faith;
6. Failure to inform relevant information to the superiors of the authority or other officials or employees who have connection with the case without due reason;
7. Refusal to provide available information, which is not regarded as a classified one to a legitimate request of an individual;

8 የሚሰጡ ውሳኔዎችን ያለበቂ ምክንያት ወይም ያለማስረጃ መስጠት ወይም እርምጃ አለመውሰድ፤

9 በሚሰራው ሥራ የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ለሚመለከተው አካል በቸልተኝነት አለማሳወቅ፤

! በትርፍ ጊዜው መሥሪያ ቤቱን ሳያሳውቅ ገቢ የሚያስገኝ ሌላ ስራ መሥራት፤

!1 በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ ክብደት ያለው የዲሲፕሊን ጉድለት መፈፀም፡፡

**፵9 ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋቶች**

በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፶6/2ሺ! እንቀጽ ፸ ከተመለከቱት በተጨማሪ የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲስፒሊን ቅጣት ያስከትላሉ፡-

1 ማንኛውንም ጥቅም ወይም ጉበ ከተገልጋዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጠየቅ ወይም መቀበል፤

2 የሥራ ኃላፊነትን በአግባቡ ባለመወጣት በባለሥልጣኑ ወይም በሦስተኛ ወገን ላይ ጉዳት ማድረስ፤

3 ሚስጥራዊ መረጃዎችን የማግኘት ሥልጣን ለሌለው ሰው አሳልፎ መስጠት፤

4 የተሰጠውን ሥልጣን ካላአግባብ በመጠቀም በግለሰብ አካል እና ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፤

5 ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በአማላጅ ወይም በማዳላት መስራት፤

8. Making decisions without sufficient reasons or evidence; failure to take measures;
9. Negligently fail to inform the encountering of a conflict of interest to the relevant organ while carrying out his job;
10. Working overtime in his leisure time without notifying the authority;
11. Committing other disciplinary offenses that have similar gravity as those stated under this Article.

**49. Offenses that Entail Rigorous Disciplinary Penalties**

In addition to the offenses stated under Article 70 of the Addis Ababa city government civil servants' proclamation number 56/2018, the following offenses shall entail rigorous disciplinary penalties:

1. Solicit or accept any kind of benefit or bribe directly or indirectly from customers;
2. Failure to carry out responsibilities and cause damage to the authority or a third party;
3. Disclose classified information to an unauthorized person;
4. Abuse his power and cause physical harm to individuals or damage their property;
5. Act as an intermediary or become biased having the intention to unfairly benefit oneself or another person;

6 የባለሥልጣኑን አገልግሎት አሰጣጥ በአግባቡ እንዳይፈጸም ማደናቀፍ፤

7 ሰውን ለመጉዳት ወይም የግል ዓላማን ለማሳካት ሆን ብሎ ትክክል ያልሆነ ክስ ማቅረብ፤

8 ማጭበርበር ወይም የማይፈጸም የተስፋ ቃል መስጠት፤

9 በባለሥልጣኑ ሠነዶች ወይም መዝገቦች ላይ ሆን ብሎ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃዎችን ማስፈር ፤

! የባለሥልጣኑን አርማ ወይም ማህተም ወይም ስም ለህገ ወጥ ተግባር መጠቀም፤

!1 ከባለሥልጣኑ ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መደለል ወይም መሰል ተግባራት ላይ ተሰማርቶ መገኘት ፤

!2 ሳይፈቀድ በባለሥልጣኑ ስም ስጦታን ወይም ዕርዳታን መጠየቅ ወይም መቀበል፤

!3 ስለሥራው አፈጻጸም ሆን ብሎ የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረብ፤

!4 የባለሥልጣኑን ስም የሚያጎድፍ ወይም ተገልጋዩ በባለሥልጣኑ ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያስደርግ ተግባር መፈጸም፡፡

## ፶ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

1 በማንኛውም ሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን ቅጣት ከመወሰዱ በፊት የፓራሚሊተሪ ሠራተኛው ፈጽሟል የተባለውን የዲሲፕሊን ግድፈት እንዲያውቀው በማድረግ እራሱን እንዲከላከል እድል ይሰጠዋል፤

6. Obstruct the proper service delivery of the authority;
7. Intentionally make false accusations to harm an individual or to achieve personal gains;
8. Carry out fraudulent activities or make false promises;
9. Deliberately attaching inaccurate information in the documents or records of the authority;
10. Use the logo or seal or name of the authority for illegal activities;
11. Brokering in connection with the works of the authority or engaging in such other similar activities;
12. Solicit or accept gifts or support on behalf of the authority without any permission;
13. Provide wrong reports about the performance of activities;
14. Commit activities that defame the authority or cause customers to lose confidence in the authority.

## 50 Taking Disciplinary Measures

1. Before taking any disciplinary measures on any employee, the paramilitary employee shall be notified of the alleged disciplinary defect to allow him to defend himself;

2 የዲስፕሊን ቅጣት የማንኛውንም ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፤

3 የዲሲፕሊን እርምጃ የፓራ-ሚሊተሪ ሠራተኛውን የወንጀልና የፍትሐብሔር ተጠያቂነት አያስቀርም፡፡

**፶1 የዲሲፕሊን ኮሚቴ ስለማቋቋም፤**

1 ባለሥልጣኑ መደበኛ የዲሲፕሊን ምርመራ የሚያካሂድና ለዋና ሥራ አስኪያጁ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያቋቁማል፤

2 የዲሲፕሊን ኮሚቴ አምስት ድምጽ ያላቸው አባላት ይኖሩታል፤ ሰብሳቢና ሁለት አባላት በዋና ሥራ አስኪያጁ ይሰየማል፤

3 ከአምስቱ ሁለት የኮሚቴ አባላት በሠራተኞች ይመረጣሉ፤ ከዚህ ውስጥ አንዷ ሴት መሆን አለባት፤

4 የባለሥልጣኑ የሰው ሀብት አስተዳደር ድምጽ የሌለው ፀሐፊ ይሆናል፤

5 የኮሚቴው አባላት የስራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፡፡

2. A disciplinary penalty could be made without waiting for or following the decision of any court;

3. The disciplinary measure does not absolve the paramilitary employee from criminal and civil liability.

**51. Establishing a Disciplinary Committee**

1. The authority shall establish a discipline committee that conducts regular disciplinary investigations and submit a decision proposal to the general manager;
2. The discipline committee shall have five voting members; the chairperson and two of the members shall be assigned by the general manager;
3. Two of the members among the five shall be elected by the employees; one should be a woman;
4. The human resource management of the authority shall be a secretary without a vote;
5. The term of office of the committee shall be two years.

**፶2 አገልግሎት ስለመቋረጥ**

1 አገልግሎት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) በገዛ ፈቃድ፣

ለ) በህመም ወይም በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት፣

ሐ) በችሎታ ማነስ፣

መ) በዲስፐሊን ምክንያት፣

ሠ) በእድሜ ወይም በሞት፣

ይሆናል፡፡

2 የፓራ ሚሊተሪ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ በመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

3 ባለስልጣኑ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ሠራተኛው ሲስማማ የፓራሚሊተሪ ሠራተኛ አገልግሎት ከጡረታ መውጫ እድሜ በኋላ ከ5 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡ አፈጻጸሙ በፐብሊስ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

**ክፍል አሥር**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፶3. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

የደንብ መተላለፉ የተፈጸመዉ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ከሆነ ቅጣቱ የሚወሰነዉ በወቅቱ ፀንቶ በነበረው ደንብ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

**52. Termination of Service**

1. A service could be terminated due to the following reasons:
   A. Resignation;
   B. Due to illness or sustained injury while on duty;
   C. Incompetence;
   D. Due to disciplinary defects;
   E. Retirement or death;
2. The retirement age of a paramilitary employee shall be determined by the civil servants' retirement directive;
3. The service of a paramilitary employee may be extended for a period of not exceeding 5 years beyond the age of retirement when the authority deems it necessary for the job and the employee agrees. The execution of such shall be determined according to the implementation directive of the public service and human resource development bureau.

**Part Ten**

**Miscellaneous Provisions**

**53. Transitional Provisions**

If the code violation was committed before the effectiveness of this regulation, the penalty shall be determined according to the active regulation of that period.

**፶4 የመተባበር ግዴታ**

ይህን ደንብ በመፈጸምና በማስፈጸም ሂደት ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፶5 ስለ ሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት**

1 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ፤ ደንብ እና መመሪያ በዚህ ደንብ ውስጥ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ካቢኔው ያወጣው ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፶6 ስለተሻሩ ህጎች**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፶4/2ሺ5 በዚህ ደንብ ተሽሯል ፡፡

**፶7 መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ባለስልጣኑ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፶8 ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመጋቢት 4 ቀን 2ሺ!5 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 4 ቀን 2ሺ!5 ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**54. Duty to Cooperate**

Any individual shall be bound to cooperate to execute or cause the execution of this regulation.

**55. Application of Other Laws**

1. The proclamation, regulation, and directives of the Addis Ababa city government civil servants shall be applied on matters that are not covered under this regulation;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, any regulation, directive, or customary practices of the cabinet which are inconsistent with this regulation shall have no effect.

**56. Repealed Laws**

The Addis Ababa city government code enforcement service regulation number 54/2012 is repealed by this regulation.

**57. Power to Issue Directives**

The authority may issue directives that are necessary for the implementation of this regulation.

**58. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 13th day of March 2023.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March 2023.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**

**<u>የቅጣት ሰንጠረዥ 1</u>**

**<u>በሕገ-ወጥ መንገድ መሬት መያዝና ህገ -ወጥ ግንባታ</u>**

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | አስተዳደራዊ እርምጃ | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ<br>1.1. የመንግስትን መሬት በማናቸውም መንገድ መያዝ፤<br>1.2. የመንግስትን መሬት በመያዝ ህገወጥ ግንባታ መገንባት፤ | መከላከል፣ ማስቆም፣ማስጠንቀቂያ መስጠት እና ወደ ህግ እንዲቀርብ መረጃውን አደራጅቶ ለሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ እንዲመሰረት ማድረግ፡፡ | ወደ ነበረበት መመለስ |
| 2 | መሬት ማስፋፋት<br>2.1. በህጋዊ መንገድ ከተያዘው የቦታ ስፋት መጠን በላይ የመንግሰት መሬት አስፋፍቶ መያዝ<br>2.1 .1 ከመኖሪያ ቤት<br>2.1.2 ከድርጅት<br>2.2. ህጋዊ ይዞታን **በማስፋፋት ህገ-ወጥ ግንባታ** መገንባት<br>2.2.1. ከመኖሪያ ቤት<br>2.2.2. ከድርጅት | መከላከል፣ ማስቆም፣ማስጠንቀቂያ መስጠት እና ወደ ህግ እንዲቀርብ መረጃውን አደራጅቶ ለሚመለከተው የፍትህ አካል ክስ እንዲመሰረት ማድረግ፡፡ | ወደነበረበት መመለስ<br>ግንባታውን በማፍረስ ወደነበረበት መመለስ |
| 3 | በሕጋዊ የመሬት ይዞታ ላይ አግባብ ካለው አካል የግንባታ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውም ግንባታ ማካሄድ<br>3.1. በፕላስተክ፣ በሸራ በመሳሰሉት<br>3.2. በብሎኬት፣ በብረት፣ በድንጋይ፣ በእንጨትና በጭቃ በመሳሰሉት<br>3.3. የቁስ፣ የመጠን ወይም የዲዛይን ለዉጥ ያደረገ እድሳት | ብር 1 ሺ<br>ብር 3 ሺ<br>ብር 2ሺ | ግንባታዉን በማፍረስ ወደነበረበት መመለስ ወይምወደህጋዊ መንገድ መግባት |
| 4 | ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛዉንም አይነት ግንባታ የቁስ፣ የመጠን ወይም የዲዛይን ለዉጥ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ እድሳት ማከናወን | ብር 300.00 | ወደህጋዊ መንገድ መግባት |

## Penalty Schedule 1

## Illegal Land Seizure and Illegal Construction

| No. | Types of Offenses | Administrative Measures | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Without having a permission from the relevant organ:<br>1.1. Possess land in any manner;<br>1.2. Possess land and carry out illegal construction | Prevent, stop, issue warning and organize evidences and send it to the relevant justice body to initiate a prosecution | Maintain the previous status quo |
| 2 | Expansion of land<br>2.1. Expand and possess land in addition to the legally provided land:<br>2.1.1. From residential houses;<br>2.1.2. From organizations;<br>2.2. Expand a legally possessed landholding and carry out illegal construction | Prevent, stop, issue warning and organize evidences and send it to the relevant justice body to initiate a prosecution | Maintain the previous status quo<br>Demolish the construction and maintain the previous status quo |
| 3 | Carry out any kind of construction on a legally possessed landholding without having a construction permit from the relevant organ:<br>3.1. Using plastics, canvas and similar other materials;<br>3.2. Using bricks, metal, stones, wood, mud, and similar other materials;<br>3.3. Renewal without making material, size, or design change; | Birr 1,000.00<br>Birr 3,000.00<br>Birr 2,000.00 | Demolish the construction and maintain the previous status quo or return to the legal system |
| 4 | Carry out any kind of renewal construction without making a material, size, or design change | Birr 300.00 | Return to the legal system |

## የቅጣት ሰንጠረዥ 2

## በሕገ-ወጥ መንገድ ፍሳሽም ሆነ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት ክፍያ መጠን | ከህገ-ወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማንኛውም ሰው ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በግቢው ውስጥ በአግባቡ አለመያዝ፤ በዓይነት አለመለየት፤ ማዝረክረክ፤ ለጤናና የአካባቢ ገጽታ በሚጎዳ መልኩ ማከማቸት፤ | | **በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ደረቅ ቆሻሻ ማንሳት** |
| | 1.1. ከመኖሪያ ቤት ከሆነ | ብር 500.00 | |
| | 1.2. ከድርጅት ከሆነ | ብር 3,000.00 | |
| 2 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት ሰጬ ድርጅት/ማህበር | | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| | 2.1. ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብ በአካባቢው ላይ ካንጠባጠበ ወይም የአካባቢውን ገጽታ ካበላሸ | ብር 300.00 | |
| | 2.2. በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኛው ተገቢውን አገልግሎት ካልሰጠ | ብር 1,000.00 | |
| | 2.3. ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እውቅና ውጬ የአገልግሎት ክፍያ ከደንበኛው ከተቀበለ | ብር 3,000.00 | |
| | 2.4. ጊዚያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ በታዎችን እስከ 5 ሜትር ዙሪያ ድረስ ጽዱ ካላደረገ | ብር 1,000.00 | |

## Penalty Schedule 2

## Illegal Disposal of Sewerage or Solid Wastes

| No. | Types of Offenses | Penalty Fee | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Anybody who does not properly handle a solid waste that he generated within his premises, identify accordingly, littering, and store it in a way that harms the health and the environment:<br>1.1. From houses<br>1.2. From organizations | <br>Birr 500.00<br>Birr 3,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 2 | Any sanitary service providing organization/association:<br>2.1. Littering while collecting solid wastes or make the surrounding messy;<br>2.2. Not properly provide service to customers based on the set standard;<br>2.3. Accept undue service charges from customers without the knowledge of the sanitary management agency;<br>2.4. Failure to clean temporary solid waste storage areas within 5 meters radius; | Birr 300.00<br>Birr 1,000.00<br>Birr 3,000.00<br>Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ እውቅና ሳይኖረው በግል፤ በማህበርም ይሁን በድርጅት ስም በግቢ ውስጥ ወይም በክፍት ቦታ ላይ ያከማቸ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማስወገድ |
| 4 | በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ የተሰማራ ግለሰብ፤ ማህበር ወይም ድርጅት ለመልሶ መጠቀምና ኡደት የዋለ ደረቅ ቆሻሻ መረጃ ለሚጠይቀው ህጋዊ አካል ካልሰጠ፤ | ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና መረጃ መስጠት |
| 5 | በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ውስጥ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የሚውል ደረቅ ቆሻሻ የለቀመ ወይም ያከማቸ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያከማቸውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 6 | ደረቅ ቆሻሻን ከግቢው አውጥቶ ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም ያስቀመጠ፤<br>6.1. የመኖሪያ ቤት ቆሻሻ ከሆነ<br>6.2. የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ከሆነ<br>6.3. የጤና ተቋም ቆሻሻ ከሆነ<br>6.4. ከሌሎች ድርጅቶች የመነጨ ቆሻሻ ከሆነ | <br>ብር 500.00<br>ብር 10,000.00<br>ብር 15,000.00<br>ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 7 | • ከመኪና ውስጥ የመነጨን ደረቅ ቆሻሻ በማንኛውም ባልተፈቀደ ቦታ ጠርጎ ከጣለ<br>• አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ከመኪና ውስጥ ሆኖ በመስኮትም ይሁን በበር በኩል ማንኛውንም ዓይነት ደረቅ ቆሻሻ ወደ ውጭ ከወረወረ ወይም ከጣለ፤ | ብር 1,000.00<br>ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | Storing solid wastes in a compound or open space for reuse or recycling purpose on individual basis, through association, or in the name of an organization without having a legal permit from the sanitary management agency; | Birr 3,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 4 | Failure to provide information for the request of an authorized body regarding the solid waste used for reuse or recycle purpose by an individual, association or organization; | Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and provide the information |
| 5 | Taking or storing solid wastes to be used for reuse or recycle purpose without having a legal license from the solid waste disposal site; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 6 | Removal of solid wastes out a compound and disposing or placing it in an authorized place;<br>6.1. If it is a household waste<br>6.2. If it is an industrial waste<br>6.3. If it is a health institution waste<br>6.4. If it is the waste of other organizations | Birr 500.00<br>Birr 10,000.00<br>Birr 15,000.00<br>Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |
| 7 | • Disposal of a waste at any place that was generated from cars;<br>• When a driver or passenger throws or removes any kind of solid waste either through the window or door while he was in the car; | Birr 1,000.00<br>Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the accumulated solid waste |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | ማንኛውም በመንገድ የሚንቀሳቀስ ሰው የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ ፌስታል፣ የጫት ገለባ፣ የፍራፍሬ ተረፈ-ምርቶች፣ የትራንስፖርት ቲኬት፣ የሞባይል ካርዶችን፣ የማስቲካና ከረሜላ ሽፋኖች፣ ወዘተ ጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ ወይም በመንገድ፤ የመንገድ ቱቦ፤ ድልድይ ውስጥ፤ በከፍት ቦታ ወዘተ ላይ ከጣለ ወይም ከወረወረ፤ | ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 9 | • ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው አሸዋ፣ አፈር፣ ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ የግንባታ ፍርስራሽ ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማስቀመጥ አካባቢን ያቆሸሸ<br>• በመንገድ ወይም በሌላ ባልተፈቀደ ቦታ ቄጠማ፤ ሳር፤ የበቆሎ፤ ጭድ፤ ሸንኮራ አገዳ፤ የሸንብራና የባቄላ እሸት፤ ፍራፍሬ ወዘተ በመሸጥ አካባቢን ያቆሸሸ ወይም ግብዓቱን ተጠቅሞ ቆሻሻ የጣለ፤ | ብር 1,000.00<br>ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 10 | አፈር፤ አሸዋ፤ ጠጠር፤ ሳርና ሌሎች ተረፈ ምርቶች በተሽከርካሪ ሲጓጓዝ በሸራ ወይም በመረብ ሳይሸፍን በመቅረቱ ምክንያት አካባቢውን ካቆሸሸ፤፡ | ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 11 | የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት/ማህበር ኤጀንሲው ለደረቅ ቆሻሻ ጊዚያ ማቆያ ወይም ማስወገጃነት ከፈቀደው ቦታ ውጭ ማንኛውንም ደረቅ ቆሻሻ ካስቀመጠ፤ ከጣለ፤ ካቃጠለ ወይም ከቀበረ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | Leaving or throwing smoked cigarettes, tissue papers, plastic bags, chat leftovers, fruit leftovers, transportation tickets, mobile card, covers of chewing gums and candies, small solid wastes, etc. on an unauthorized places, roads, sewerage lines, in bridges, higher place, and etc . | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 9 | • Placing sands, soils, grass, leaves, construction dumps in an unauthorized place without having a legal permit from the concerned organ and making the place messy;<br>• Selling grass, maize, straw, sugarcane, beans, peas, fruits, etc on streets or other unpermitted places and making the place messy or use it and remove the wastes of the thereof; | Birr 1,000.00<br><br>Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 10 | Failure to cover soil, sand, gravel, grass, and other by-products with canvas or net while transporting it and make the place messy; | Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 11 | When a sanitary service providing organization/association places, dumps, burns, or buries any solid waste except the places where the agency allows for the temporary placement or disposal of solid wastes; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | ከመፀዳጃ ቤት ውጭ በማንኛውም ቦታ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት | ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 13 | በመንገድ ዳር በሚቀመጡ የጥቃቅን ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ እቃዎችን<br>9.1. ያለ ህጋዊ ፈቃድ ከአካባቢው ያስወገደ፤ ነቅሎ የጣለ፤ ያበላሸ፤ የሰበረ፤ የወሰደ፤ ለሌላ አገልግሎት ያዋለ<br>9.2. ማስታወቂያ የለጠፈ ወይም በላያቸው ላይ እቃ ያስቀመጠ | ብር 20,000.00<br>ብር 500.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንብረቱን መመለስ ወይም ማስታወቂያውን ማንሳት |
| 14 | በአገልግሎት ሰጭ ተቋማትና የማምረቻ ድርጅቶች ተገቢ የሆነ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ በግቢው ውስጥና በአካባቢው አለማስቀመጥ፤ | ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ደስት ቢን ማስቀመጥ |
| 15 | ከቤት እንስሳት የሚወጡ እዳሪ (ኩስ፤ ፍግ፤ እበት)፤ እና የእንስሳት የምግብ ተረፈ ምርቶችን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ወይም አካባቢውን ያቆሸሸ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳትና አካባቢውን ማጽዳት |
| 16 | የተለያዩ እንስሳትን ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በማጸዳዳት አካባቢውን ማቆሸሽ በአንድ እንስሳ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንዲከፍል ይደረጋል፤ | ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻ ማንሳት |
| 17 | ሳር፤ ቅጠላ ቅጠል፤ አፈር፤ አሸዋና ሌሎች ተረፈ ምርቶችን ሳይሸፍን በጋማ ከብት በማጓጓዝ አካባቢውን ያቆሸሸ ወይም ያዝረከረከ | ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | Peeing or defecating on any place except from toilets; | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the place |
| 13 | Concerning the litterbins that placed on road sides:<br>14.1. Removes, dislocates and throws away, damages, breaks, takes, or uses it for another purpose;<br>14.2. Post advertisements or puts things on it; | Birr 20,000.00<br><br>Birr 500.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and return the property or remove the advertisement |
| 14 | The failure of service providing institutions and manufacturing organizations to place appropriate litterbins within their compound and the surrounding area; | Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and prepare litterbins |
| 15 | Removing wastes of domestic animals and the by-products of their fodders on an unauthorized place or make the place messy; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the disposed waste and clean the place |
| 16 | Allowing various animals defecate on an unauthorized place and make the place messy; (forced to pay the indicated fine per head) | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 17 | Failure to cover grass, leaves, soils, sand, and other by-products while transporting it by equine and making the place messy or littering; | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 18 | የሞተ እንስሳን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ | ብር 200.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 19 | የአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማዕከላትና የተለያዩ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ ሰዎችና ድርጅቶች የተረፈ ምርታቸውን ደረቅ ቆሻሻ<br>20.1. ከንግድ ማዕከሉ ግቢ ውጭ ወይም መንገድ ዳር ተረፈ ምርት ቆሻሻ ያከማቸ ያስቀመጠና የጣለ፤<br>20.2. ከተሽከርካሪ ላይ አትክልትና ፍራፍሬ ሲጭንና ሲያወርድ የሚወዳድቁ የአትክልት ትርፍራፊ ቆሻሻ ወዲያው ያላጸዳ፤<br>20.3. የገበያ ማዕከሉን ደረቅ ቆሻሻ በራሱ ወጭ ሰብስቦ ኤጀንሲው በፈቀደው ህጋዊ ማስወገጃ ቦታ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማእከላት ያላስወገደ፡፡<br>20.4. ከመደብሩ ፊት ለፊት የመደብር ጥራጊ፤ በሽያጭ ወቅት የተከሰቱ የእቃ ማሸጊያ፤ የጫት ገራባ፤ ካርቶን ወዘተ ካስቀመጠ፤ | ብር 2,000.00<br>ብር 200.00<br>ብር 5,000.00<br>ብር 300.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 18 | Disposal of dead animals on an unauthorized place | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 19 | Regarding the solid wastes of the by-products of individuals and organizations that are working in vegetable and fruit markets and in various business centers: | | |
| | 20.1. Accumulating, placing, and disposing solid wastes outside the compound of the business center or on road sides; | Birr 2,000.00 | |
| | 20.2. Failure to immediately clean leftover wastes while loading and unloading vegetables and fruits from vehicles; | Birr 200.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| | 20.3. Failure to collect solid wastes of the business center at its own cost and dispose it at an authorized disposal site or reuse and recycle center by the agency; | Birr 5,000.00 | |
| | 20.4. Placing wastes of the shop, wrapping materials generated during exchange, chat wastes, cartoons, etc. in front of the shop; | Birr 300.00 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20 | • ከግንባታ ወይም ከፍርስራሽ የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ግለሰብ/ድርጅት<br>• በከግንባታ ማዕከል በተሽከርካሪ ጎማ እንቅስቃሴ ወይም በጭነት ወቅት በሚንጠባጠብ አፈር፤ ጭቃ፤ ፍርስራሽ ወዘተ ምክንያት በሚፈጠር ቆሻሻ አካባቢውና መንገዱ ያበላሸ የግንባታ ባለቤት | ብር 5፣000.00<br>ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 21 | የአጥንትና የስጋ ተረፈ ምርትን ባልተፈቀደ ቦታ የጣለ ግለሰብ/ድርጅት | ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 22 | ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህጋዊ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ወይም ተገቢነት የሌለውን ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከል፤ ቅብብሎሽ ጣቢያ ወይም የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከል ያጓጓዘ ድርጅት/ማህበር/ግለሰብ/ተቋም፤ | ብር 10,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያመጣውን ቆሻሻ መመለስ |
| 23 | አገልግሎት የማይሰጡ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶችን በተለየ መልኩ በመለየት በአግባቡ እና አካባቢውን በማይበክል መንገድ እንዲወገድ ካላደረገ፡ | ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና የጣለውን ቆሻሻ ማንሳት |
| 24 | ከመኖሪያ ቤት ወይም ከድርጅት ግቢ ውጭ ያለውን የአካባቢ ንጹህና አረንጓዴ አድርጎ አለመጠበቅ<br>25.1. ከመኖሪያ ቤት አጥር ግቢ ውጭ እስከ 5 ሜትር ርቀት አለማጽዳት፤<br>25.2. ከድርጅት/ተቋም አጥር ግቢ ውጭ እስከ 5 ሜትር አለማጽዳት፤ | ብር 300.00<br>ብር 5,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20 | • An individual/organization that removes wastes generated from construction or demolishes on an unauthorized place;<br>• A construction owner that harms the surrounding and roads as a result of the movement of cars or loading of soils, mud, demolishes etc. | Birr 5,000.00<br><br>Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 21 | Disposal of bone and meat by-products in an unauthorized place; | Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 22 | Transporting any dangerous or inappropriate solid waste to a disposal site, incinerator, transfer station, or reuse and recycle center without the permission of the sanitary management agency; | Birr 10,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and take back the waste |
| 23 | Failure to identify used electronic equipment in a special manner and remove it properly in a way that will not harm the environment; | Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and remove the waste |
| 24 | Failure to make the area which is found outside of a house or organization green and clean and preserve same:<br>25.1. failure to clear the area outside of the house up to 5 meters radius;<br>25.2. failure to clean the area outside of an organization/institution up to 5 meters radius; | Birr 300.00<br><br>Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25 | ወቅታዊና ልዩ ዝግጅት አከናውኖ በዓሉ ሲጠናቀቅ በዕለቱና ወዲያው ዝግጅቱ የተከናወነበትን አካባቢ ከቆሻሻ ያላጸዳ የፕሮግራሙ አዘጋጅ፤ | ብር 5,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 26 | ዓመታዊ፤ ወርሃዊና ሳምንታዊ የእምነት በዓላት ሲከናዎኑ ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ የዝግጅቱ ባለቤት በዕለቱና ወዲያው አካባቢውን ካላጸዳ፤ | ብር 3,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ያቆሸሸውን አካባቢ ማጽዳት |
| 27 | የታክሲና ሚኒባስ ተራ አስከባሪዎች፤ የፓርኪንግ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች፤ በጫማ ጥገናና ጽዳት (ሊስትሮ) የተሰማሩ፤ በእረፍት ቀን (ቅዳሜና እሁድ) መንገድ ላይ የሚነግዱ ነጋዴዎች፤ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው የእንስሳት የግብይት ማዕከላት ወዘተ የሚሰሩበትን አካባቢ እስከ 5 ሜትር ዙሪያ ከቆሻሻ ጽዱ ያላደረገ ማህበር/ግለሰብ፤ | ብር 500.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ማጽዳት |
| 28 | የባቡር ሀዲድ የተዘረጋባቸውን መስመሮችና የባቡር ፌርማታዎች ከደረቅ ቆሻሻ እንዲጸዳ ያላደረገ የባቡር ድርጅት፤ | ብር 5,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና አካባቢውን ከቆሻሻ ማጽዳት |
| 29 | • የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የእምነት ተቋማት፤ ትምሀርት ቤቶች፤ ንግድ ድርጅቶች፤ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች፤ ኢምባሲዎች ሰራተኞቻቸውን አስተባብረው በጽዳት ንቅናቄው ተሳታፊ ያላደረገ ተቋም/ድርጅት፤<br>• የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው የጽዳት ንቅናቄ መመሪያ መሰረት በመኖሪያ አካባቢው በጽዳት ንቅናቄ ተሳታፊ ያልሆነ አባወራ ወይም እማወራ፤ | ብር 2,000.00<br>ብር 300.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና በንቅናቄ ተሳታፊ መሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25 | An event organizer that organized a timely event and special program who failed to clean the area where the event took place on that same day and immediately after the completion of the program; | Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 26 | When the concerned owner of a program fails to clean the area, immediately and on the same day, where an annually, monthly, and weekly religious holiday is celebrated; | Birr 3,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 27 | Taxi and mini-bus queue controllers, parking service providing organizations, shoe-shiners, weekend street vendors, cattle trading market centers, etc. and organizations/individuals that fail to clean an area of 5 meters radius; | Birr 500.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 28 | A railway organization that fails to clean solid wastes from the railway lines and train stations | Birr 5,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and clean the area |
| 29 | • Government offices, non-governmental organizations, religious institutions, schools, business entities, service providing institutions, embassies or an institution/organization that are unable to coordinate its employees and fail to participate in cleaning campaigns which are organized according to the cleaning campaign directive to be issued by the sanitary management agency;<br>• A household that fails to participate in cleaning campaigns which are organized according to the cleaning campaign directive to be issued by the sanitary management agency; | Birr 2,000.00<br>Birr 300.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and participate in the campaign |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 30 | ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት/ማህበር/ተቋም ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ሰራተኞቹ/አባላቱ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ሳይጠቀም አገልግሎት ከሰጠ ወይም ንጽህናውን ያልጠበቀ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት ተጠቅሞ አገልግሎት ከሰጠ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ንጹህ የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት መጠቀም |
| 31 | • ማንኛውም የጽዳት አገልግሎት የሚሰጥ የጽዳት ድርጅት በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ያልተፈቀደ ደረቅ ቆሻሻ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም ማዕከል ወይም ወደ ማቃጠያ ማዕከላት አጓጉዞ ካመጣ፤<br>• ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ፈቃድ ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውጪ ወደ ከተማው ያስገባ፤<br>• በመረብ ወይም በሸራ ያልተሸፈነ ደረቅ ቆሻሻ በተሽከርካሪ ጭኖ ወደ በማስወገጃ ቦታ፤ መልሶ መጠቀም ማዕከል ወይም ማቃጠያ ማዕከላት አጓጉዞ ያመጣ ድርጅት /ማህበር/ ግለሰብ/ ተቋም፤ | ብር 10,000.00<br>ብር 20,000.00<br>ብር 1,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈልና ቆሻሻውን ወደ መጣበት ቦታ መመለስ |
| 32 | ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት ወይም ማህበር ከተመደበበት የስራ ቦታ ወይም ምደባ ውጭ ደረቅ ቆሻሻ ከሰበሰበ፤ | ብር 2,000.00 | በሰንጠረዡ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ መጠን መክፈል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 30 | The failure of any sanitary service providing organization/association/institution to make sure that its employees/members are using safety materials and provide service as per the standards to be issued by the agency or use materials that are below the standard and provide service; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and use clean safety materials |
| 31 | • Any sanitary service providing organization that transports and brings unauthorized solid waste by the sanitary management agency to the disposal site, reuse and recycle center or incinerator;<br>• Bringing solid wastes out of the vicinities of the Addis Ababa city administration without the permission of the sanitary management agency;<br>• An organization/association/individual/institution that fails to cover a solid waste using net or canvas and transport and bring it to disposal sites, reuse and recycle centers or incinerator; | Birr 10,000.00<br>Birr 20,000.00<br>Birr 1,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule and return the solid waste back to its place of departure |
| 32 | When any private sanitary service providing organization or association collects solid wastes out of its allocated working area or assignment; | Birr 2,000.00 | Pay the fine indicated in the penalty schedule |

**የቅጣት ሰንጠረዥ 3**

**የትራፊክ እንቅስቃሴና የመንገድ ደህንነት የሚጐዱ ተግባራት መፈጸም**

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን ክፍያ | ከህገወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ወዘተ መንገድ ላይ ማራገፍ | ብር 2,000.00 | ማንሳት |
| 2 | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ብረት፣ እንጨት ወይም ድንጋይ በመንገድ ላይ መፍለጥ፣ ማስፈለጥ፣ ወይም መጥረብ፣ ማስጠረብ<br>2.1 ሠራተኛ<br>2.2 አሰሪ | ብር 50.00<br>ብር 500.00 | ማንሳት አካባቢዉን ማጽዳት |
| 3 | በመንገድ ላይ ጭቃ ማቡካት ወይም ማስቦካት ወይም ማንኛውም መሰናክል ማድረግ<br>3.1ሠራተኛ<br>3.2አሰሪ | ብር 50.00<br>ብር 500.00 | ከመንገድ ማንሳት አካባቢዉን ማጽዳት |
| 4 | ማንኛውም ሰው በሕጋዊ መንገድ ከያዘው ይዞታ ውጭ በመሆን መንገድን ወይም በማስተር ፕላኑ መሠረት ለመንገድነት የተያዙ ክፍት ቦታ ዕፅዋት መትከል፣ "ማቆም ክልክል ነው" የሚል ጽሁፎችን ወይም መሰል ምልክቶችንም ሆነ ማናቸውንም ግንባታ ማቆም፣ ቤት መሥራት፣ አጥር ማጠር፣ | ብር 3,000.00 | ወደነበረበት መመለስ |
| 5 | አውቆም ሆነ በድንገተኛ ሁኔታ በድልድዮች፣ በመንገድ መብራቶችና ቋሚዎች (ፖሎች)፣ በትራፊክ ምልክቶች፣ በትራፊክ መብራቶች በእግረኛ መከላከያዎች፣ በማንሆሎች፣ በፍካዎች ወይም በክዳኖቻቸው ላይ ጉዳት ማድረስ፣ | ብር 500.00 | ጉዳት የደረሰባቸዉ ንብረቶችን መጠገን ወይም መተካት |
| 6 | በህገወጥ መንገድ መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር፣ መቀየስ፣ ማናቸዉምንም መንገድበበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር፣ድንጋይ መደርደር፣መንገድ መቁረጥ፣ መስበር፣ መቆፈር ወይም በሌላ ሁኔታ ተሽከርካሪ ወይም እግረኛ እንዳይተላለፍ ማድረግ | ብር 1,000.00 | ወደ ነበረበት መመለስ |
| 7 | የዋና መንገዶች በማናቸውም ምክንያቶች አለመዘጋት እንደተጠበቀ ሆኖ በኅዘን ምክንያት ሳይሆን የእግረኛንም ሆነ የተሽከርካሪን መንገድ ድንኳን በመጣል (በመትከል) በከፊልም ሆነ በሙሉ መዝጋት፣ | ብር 200.00 | መንገዱን ክፍት ማድረግ |

## Penalty Schedule 3

## Carry out Activities that Hinder Traffic Movement and Harm Road Safety

| No. | Types of Offenses | Penalty Fee | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Placing stones, sand, soil, etc. on the road for construction or any other purpose; | Birr 2,000.00 | Remove the material |
| 2 | Weld, cut, or carve or cause the welding, cutting, or carving of metal, wood, or stone for construction or any other purpose:<br>2.1. Employee<br>2.2. employer | Birr 50.00<br>Birr 500.00 | Remove the material and clean the area |
| 3 | Mix or cause the mixing of mud on road or place any other kind of obstacle;<br>1.1. Employee<br>1.2. Employer | Birr 50.00<br>Birr 500.00 | Remove the material from the road and clean the area |
| 4 | Anybody who plants seedlings on vacant spaces that are intended for road purpose based on the master plan beyond his legal possession, placing "No Parking" signs or any other writings or signs, carry out constructions, making houses, and compounds; | Birr 3,000.000 | Return to its former status |
| 5 | Deliberately or indeliberately damage bridges, street lights (poles), traffic signals, traffic lights, pedestrian barriers, manholes, sewer openings or their closings; | Birr 500.00 | Repair or replace the damaged properties |
| 6 | Improve, change, or design roads in an illegal manner, close any road using doors, make fences, close it with stones, cut and dig roads, or obstruct the passage of vehicles or pedestrians in any other way; | Birr 3,000.000 | Return to its former status |
| 7 | Without prejudice to not closing main roads in any circumstances, closing pedestrian or vehicle roads, totally or partially, by making tents, not due to mourning; | Birr 200.00 | Open the road |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | በመንገድ ላይ የግንባታ ተረፈ ምርት ውጤቶችን መድፋት | ብር 1,000.00 | የደፋውን ማንሳት |
| 9 | ሆን ብሎ የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ ከመንገድ ጋር ማገናኘት ወይም በማናቸዉም ሁኔታ መልቀቅ | ብር 1,000.00 | ወደነበረበት መመለስ |
| 10 | መንገድ ላይ የተበላሸ ተሽከርካሪ መጠገን ወይም ማስጠገን<br>10.1. መጠገን<br>10.2. ማስጠገን | ብር 500.00<br>ብር 1,000.00 | ተሽከርካሪዉንማንሳት |
| 11 | በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ማጠብ ወይም ማሳጠብ<br>11.1. ማጠብ<br>11.2. ማሳጠብ | ብር 50.00<br>ብር 200.00 | የቆሸሸውን ማጽዳት |
| **12** | ከይዞታው ውጪ የጋራዥ አገልግት ወይም ጥገና<br>9.1. የሚያደርግ ግለሰብ ወይም ድርጅት<br>9.2. የሚያስጠግን | <br>ብር 3,000.00<br>ብር 200.00 | ተሽከርካሪዉን ማንሳት እና በታውን ማፅዳት |
| **13** | በተወሰኑ ቀናትና ሰዓት የንግድ ስራን ለመነገድ ተለይተው ከተፈቀዱበት መንገዶች በስተቀር የንግድ ሥራን በመንገድ ላይ ማካሄድ፣ | ብር 500.00 | |
| **14** | ለንግድ አገልግሎት ከተፈቀደ ይዞታ ውጭ በእግረኛ መንገድ ላይ ንግድ መነገድ | ብር 5,000.00 | |
| **15** | በክፍት ወይም ዝግ የመናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ አካፋዬች፣ የመንገድ ዳርቻዎች፣ አደባባዬች ላይ ያሉ ሳሮችን፣ ችግኞችን ወይም የመሳሰሉትን ዕጽዋት መቁረጥ፣ መርገጥ ወይም ማበላሸት | ብር 100.00 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | Dumping of construction wastes on roads | Birr 1,000.00 | Remove the dumped wastes |
| 9 | Deliberately connect toilet lines with roads or discharge wastes in any circumstances; | Birr 1,000.00 | |
| 10 | Repair or cause the repairing of cars on the street<br>10.1. Repair<br>10.2. Cause the repairing | <br>Birr 500.00<br>Birr 1,000.00 | <br>Remove the car |
| 11 | Wash or cause the washing of a car on the street<br>11.1. Washing<br>11.2. Cause the washing | <br>Birr 50.00<br>Birr 200.00 | <br>Clean the dirt |
| 12 | Providing garage service or repair cars outside of the legal premises<br>12.1. Individual or organization<br>12.2. Someone that causes the repairing | <br>Birr 3,000.00<br>Birr 200.00 | Remove the car and clean the area |
| 13 | Undertake street vending except the determined dates and hours to carry out the street trade on permitted roads; | Birr 500.00 | |
| 14 | Carry out business activities on pedestrian roads beyond the permitted possession for a business; | Birr 5,000.00 | |
| 15 | Cutting, standing on, or damaging grasses, seedlings, or similar plants that are found at open and closed recreational places, street dividers, road sides, and roundabouts; | Birr 100.00 | |

## የቅጣት ሰንጠረዥ 4

## ህገወጥ የዉጭ ማስታወቂያ

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን ክፍያ | ከህገወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | በመንገድ ላይ ባሉ የትራፊክ መብራቶች፣ ምልክቶች፣ፖሎች ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ ወይም ማንጠልጠል፣ | ብር 1,000.00 | ማስታወቂያዎችን ማንሳት |
| 2 | በመንገዶች፤ድልድዬች ፣በእግረኛ መከላከያ አጥሮች ላይ ያለፈቃድ ማስታወቂያ ወይም ባነር መለጠፍ ወይም ማንጠልጠል፣ ወይም መትከል | ብር 1,000.00 | ማስታወቂያዎችን ማንሳት |
| 3 | ያለፈቃድ ማንኛዉንም ማስታወቂያ፣ በበራሪ ወረቀት፣ በብሮሸር ወይም በማንኛዉም መንገድ ማሰራጨት ወይም እንዲሰራጭ ማድረግ<br>3.1 አሰራጭ ግለሰብ<br>3.2 አሳታሚ ድርጅት /የማስታወቂያው ባለቤት | <br><br>ብር 50.00<br>ብር 500.00 | የሚያሰራጨዉን ማቆም |

## Penalty Schedule 4

## Illegal Outdoor Advertisements

| No. | Types of Offenses | Penalty Fee | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Posting or hanging on advertisements on traffic lights, signs, and poles on the road | Birr 1,000.00 | Removing the advertisement |
| 2 | Posting or hanging or erecting advertisements or banners on roads, bridges, pedestrian barriers without permission; | Birr 1,000.00 | Removing the advertisement |
| 3 | Distribute or cause the distribution of any advertisement through fliers, brochures, or any other means without permission: | | Stopping the distribution |
| | 3.1. Distributor | Birr 50.00 | |
| | 3.2. Printing organization/owner of the advertisement | Birr 500.00 | |

## የቅጣት ሰንጠረዥ 5

## አዋኪ ድርጊት እና መሰል ተግባራትን መፈጸም

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን ክፍያ | ከህገወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | በማንኛውም ቦታ ላይ ገቢ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ጫት ማስቃም | ብር 5,000.00 | ማስቃሙን ማቆም |
| 2 | በክፍት ወይም ዝግ የመናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ አካፋዬች፣ የመንገድ ዳርቻዎች፣ አደባባዬች ላይ ጫት መቃም<br>• እያንዳንዱ ጥፋቱን የፈጸመ ግለሰብ | ብር 100.00 | መቃሙን ማቆም እና ቦታውን ማፅዳት |
| 3 | በማንኛውም ቦታ ላይ ገቢ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ሺሻ ማስጨስ | ብር 10,000.00 | ሺሻ ማስጨሱን ማቆም |
| 4 | በትምህርት ተቋማት ዙሪያ **ሁለት መቶ ሜትር** መጠነ ዙሪያ/ ሬዴየስ/ ክልል ውስጥ፡-<br>4.1. ፊልም ወይም ቪዲዮ ማሳየት<br>4.2. የቀንም ሆነ የሌሊት የጭፈራ ተግባር ማከናወን<br>4.3. ማንኛውንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ መሸጥ<br>4.3.1 ድርጅት ከሆነ<br>4.3.2 መኖሪያ ቤት /ግለሰብ/ ከሆነ<br>4.4 ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት<br>4.5 ራቁት ዳንስ የሚያከናውን ድርጅት<br>4.6 ፔኒሲዮን ቤት መክፈት<br>4.7 ማሳጅ ቤት መክፈት | ብር 2,000.00<br>ብር 10,000.00<br><br>ብር 2,000.00<br>ብር 1,000.00<br>ብር 15,000.00<br>ብር 10,000.00<br>ብር 10,000.00<br>ብር 15,000.00 | ህገወጥ ድርጊቱን ማቆም |
| 5 | ለአዋኪ ድርጊት እና መሰል ህገ ወጥ ተግባራትን ለሚፈጽሙ ተከራይ ንብረታቸውን የሚያከራዩ | ብር 3,000.00 | |

## Penalty Schedule 5

## Carry out Disturbing Activities and Similar Actions

| No. | Types of Offenses | Penalty Fee | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Cause the chewing of chat in any place for getting or allowing other to get an income | Birr 500.00 | Stopping the chat chewing activity |
| 2 | Chewing chat in closed recreational spaces, street dividers, road sides, and roundabouts<br>• Every individual that commits the offense | Birr 100.00 | Stop the chat chewing and clean the place |
| 3 | Cause the smoking of shisha in any place for getting or allowing other to get an income | Birr 10,000.00 | Stopping the shisha smoking |
| 4 | Within the 200 meters radius of schools:<br>4.1. Showing films or video;<br>4.2. Carrying out dancing activities during the day or at night;<br>4.3. Selling on any alcoholic drinks;<br>4.3.1. If it is a business entity<br>4.3.2. If is a residential house (individual)<br>4.4. Gambling or undertake gambling activities;<br>4.5. A business entity that carry out striptease;<br>4.6. Opening pension;<br>4.7. Opening massage business; | <br>Birr 2,000.00<br>Birr 10,000.00<br><br>Birr 2,000.00<br>Birr 1,000.00<br><br>Birr 15,000.00<br>Birr 10,000.00<br>Birr 10,000.00<br>Birr 15,000.00 | Stopping the illegal activity |
| 5 | Leasing their properties to those individuals that carry out disturbing activities and such other similar illegal activities; | Birr 3,000.00 | |

## የቅጣት ሰንጠረዥ 6

## የእንስሳት ዝውውር፣ ግብይት፣ ወይም ዕርድ፣

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን ክፍያ | ከህገወጥ ድርጊት ፈጻሚዉ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ህገወጥ እርድ<br>1.1 ህገ-ወጥ እርድ እያረደ ወይም እያሰረደ የሚያቀርብ<br>1.2 ተጠቃሚ ግለሰብ<br>1.3 ተጠቃሚ ድርጅት<br>1.4 አራጅ ግለሰብበ እያንዳንዱ በአረደው ከብት ብዛት | ብር 15,000.00<br>ብር 1,500.00<br>ብር10,000.00<br>ብር 300.00 | |
| 2 | በመንገድ ላይ ከብት ማሰማራት፣ የከብት ንግድ፣ የእንስሳት ዝዉዉር ወይም ግብይት ማካሄድ<br>• በእያንዳንዱ የከብት (የእንስሳት) ብዛት | ብር 60.00 | |
| 3 | ህገወጥ የስጋ ዝዉዉር | ብር 1,500.00 | |

## Penalty Schedule 6

## Circulation, Trading, or Slaughtering of Animals

| No. | Types of Offenses | Penalty Fee | What is expected from the Transgressor |
|---|---|---|---|
| 1 | Illegal slaughtering<br>1.1. Carry out or cause the carrying out of illegal slaughtering and distribute meat;<br>1.2. Individual that use same;<br>1.3. Business entity that use same;<br>1.4. A person that slaughter the number of animal he slaughtered; | Birr 15,000.00<br>Birr 1,500.00<br>Birr 10,000.00<br>Birr 300.00 | |
| 2 | Allowing animals to graze on the road, carry out animal trading, circulation or business<br>• As per the number of cattle (animal) | Birr 60.00 | |
| 3 | Illegal meat trafficking | Birr 1,500.00 | |